“በመቅደሱ ኑር።” መቅደስ የጌታ ቃል ኪዳንና ክብር ያለበት ቦታ ነው። በእውነተኛ በረከት የተነካ አገልጋይ ከቃል ኪዳኑ ዞር አይልም። ለዚህ ነው ዳዊት “እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፣ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ።” (መዝ. 26:4) ያለው። ይህ ነው የእውነተኛ እድገት ምልክት። አንተስ የት ነህ?



# ክፍል - ሁለት

# በፍቅር ማደግ



# ምዕራፍ አምስት ከሁሉም የሚበልጥ መንገድ





## ም ዕ ራ ፍ   አ ም ስ ት

## ከ ሁ ሉ ም  የ ሚ በ ል ጠ ው  መ ን ገ ድ

ከእግዚአብሔር ቃል መከፈቻ ጥቅስ 1ቆሮ. 12:27-13:13። የ1ኛ ቆሮ. 12 መደምደሚያ ላይ ሐዋርያው በመልእክቱ ውስጥ የአንባቢዎችን ልብን በሚያቋምጥ አገላለጽ፣ አንጠልጥሎ የተወው ሃሳብ ይገኛል። ይህም ከሁሉም የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ እንድንፈልግ ካደፋፈረ በኋላ፣ ያንንም "እነግራችኋለሁ" በማለት ነው ሃሳቡን ለጊዜው (ለአፍታ) ገታ የሚያደርገው።

ለመሆኑ በአገልግሎትም ሆነ በኑሮ ውስጥ ከሁሉ የሚበልጠው መንገድ ምንድነው? ሐዋርያው ጳውሎስም፣ መልእክቱን በጊዜው ለተጻፈላቸው ለቆሮንቶስ ሰዎች ሊያሳውቅ የሚሻው ይህንኑ ዋናና ከሁሉ የሚበልጠውን፣ በእግዚአብሔርም ፈቃድ ውስጥ እጅግ ትኩረት (አጽንኦት) የተሰጠውን ጉዳይ ነው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በዘመኗ በውስጧ ያከማቸቻቸው ድክመቶች ክርታታይቷ ቤተ ክርስቲያን እስከ መሰኘት ያደረሳት እንደ ነበረ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተለይ ሁለቱንም የቆሮንቶስ መልእክቶችን ያጠኑ ሰዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን በሚጽፍበት ወቅት የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን በጅምላ ብቻ ተመልክቶ አልነበረም። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ከእድገትና ከመለወጣቸው እውነት በመነሳት በ3 ዓበይት ክፍሎች በመመደብ፣ እንደ አግባባቸው መልእክቱን ይቀበሉ ዘንድ ሁኔታዎችን ሲያመቻች እንመለከታለን። በዚህም መሠረት አንዳንዶቻችሁ ፍጥርታዊያን ናችሁ፤ ብሎ ይመድባቸዋል። ይህንን በ1ኛ ቆሮ. 2 ውስጥ ማግኘት

እንችላለን። በሐዋርያው አመዳደብ፣ ፍጥረታዊያን ማለት ያልዳኑ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያልነካቸው፣ ነገር ግን ዝም ብለው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ፣ እንደ ሌሎች የውስጥ መነካትና መለወጥ ያልጎበኛቸው፣ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። ይህንን የምደባ እውነት፣ ዛሬ ከራሳችንና ካለንበት ዘመን ጋር አመሳክረን ስንመለከተው፣ ሰዎች በዚያን ዘመንም ይሁን ዛሬ፣ እኛ በምንገኝበት ዘመን፣ የውስጥ መነካትና መለወጥ ሳይኖራቸው፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳይዳስሳቸው፣ እንደው በጅምላ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው ለመኖር የሚያደርጉትን ጥረት ጉልህ አድርጎ ማሳየቱን ማጤን ይኖርብናል። በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ፤ እውነተኛ ለውጥ ማለት ካገኙት ጋር በመሆን፣ አበረው መኳዛቸው ነው። ይህ ሁኔታቸው በእርግጥም ለደህንነታቸው ዋስትና የሚሰጣቸው መስሎ ነው የሚታያቸው። እውነቱ ግን እንደዛ አይደለም። እያንዳንዳችን በሌሎች ጥላ በመታጎርና፣ መስለን በማደር የምናገኘው ትርፍ የለም። የእግዚአብሔር መንፈስ እከሌ -ከ- እከሌ ሳይል የሁሉንም ልብ መንካት፣ መዳሰስና መለወጥ ስለሚሻ፣ በፈቃደኝነት ልባችንን ከፍተን ይገባ ዘንድ መጋበዝ ብቻ ነው ብቸኛ አማራጭ ሊሆን የሚችለው።

የእግዚአብሔር ቃል ዋቢ በማድረግ ምሳሌ መስጠት ቢያስፈልግ፣ በዘጸአት ላይ ተጽፎ በሚገኘው የእስራኤላውያን ከግብጽ እርነት የመውጣት ታሪክ ላይ እነዚህ ሕዝቦች ግብጽን ለቀው ሲወጡ፣ ከእነርሱ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች አብረዋቸው ተቀላቅለው የወጡ ግብጻውያን እንደ ነበሩ ተጽፏል። እነዚህ ግብጻውያን እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ ግብጻውያን እንደሆኑ ዕድሚያቸውን ፈጸሙ እንጂ፣ እስራኤላውያንን ተከትለውና ተቀላቅለው በመውጣታቸው ብቻ የእስራኤላዊነትን የልደትና የመሳሰሉትን መብትና ጥቅም ማግኘት አልቻሉም። እነርሱ መቸም ቢሆን ግብጻውያን ናቸውና። ልክ እንደዚሁ ተፈጥሮአዊያን በማለት ሐዋርያው የሰየማቸው ሰዎችም ከእውነተኛዎቹ ክርስቲያኖች ጋር በመደባለቃቸውና ቤተ ክርስቲያን በመመላለሳቸው ብቻ፣ ደህንነትን አግኝተዋል ማለት አይደለም።



ስለዚህ የተፈጥሮአዊያን ተቀላቅሎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመገኘት መሞከር አዲስ ነገር ሆኖ አይደለም። ገና እስራኤላውያን ታላቅ ሕዝብና መንግሥት ሆነው ራሳቸውን ከማቋቋማቸው በፊት ጀምሮ፣ የምናገኛቸው ሰዎች ናቸው። ምን ጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር ሥራ በሚሠራበት ቦታ ሁሉ፣ በሥራው ላይ የሚያሳዩት ትብብር ለደህንነታቸው ዋስትና እንደሚሆን አድርገው የሚገምቱ በርካታ ሰዎች እንደሚኖሩ ልናውቅ ይገባል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለተኛዎቹን ሰዎች ሲመድብ "ሥጋውያን" በማለት ይሰይማቸዋል። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ የነካቸው፣ ፍቅሩ የገባቸው፣ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሲሰበክ በደስታ አምነው የተቀበሉ ቢሆኑም ግን፤ ማደግ ሲገባቸው ከርሞ ጥጃ በመሆን የመንፈሳዊ ሕይወታቸው የቆረቆዘ ሰዎች ናቸው። ሥጋዊያን ክርስቲያኖች የተለወጡ ናቸው ግን በዚያው አንጻር ደግሞ በሕይወታቸው እድገት የማይታይባቸው ናቸው። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መጐልመስ ሲገባቸው፣ በሕጻንነት የተወሰኑ፣ አስተማሪዎች መሆን ሲገባቸው ተማሪ ብቻ በመሆን ዘመናቸውን የሚገፉ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ሕጻንነታቸውንና፣ ገና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጨቅላ መሆናቸውን ለማስገንዘብ "ገና ወተት ጋትኋችሁ።" በማለት በአስደናቂ ምሳሌ ያሉበትን ደረጃ አሳይቷቸዋል።

እነዚህ ሥጋዊያን ክርስቲያኖች ከሌሎች ተለይቶ ጎላ ብሎ የሚታይባቸው ባሕርይ አለ። ይኸውም ሥጋዊያን ምንም እንኳ የተለወጡ ክርስቲያኖች ቢሆኑም፣ ብዙውን ጊዜ በፈቃዳቸው፣ በውሳኔያቸው፣ በምርጫቸውና በአካሄዳቸው ላይ ቅድሚያ ሲሰጡት የሚታየው ለሥጋ ጉዳይ ብቻ ነው። የሥጋን ምሪት ማከናወን ይቀናቸዋልና ለዚህም ነው ሥጋዊያን ተብለው ሊጠሩ የሚገባቸው። በመሠረቱ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናቸው መጠን፣ በመንፈስ ፈቃድና ምሪት ውስጥ መኖር ነበረባቸው።

ሦስተኛዎቹ ዓይነቶች ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ "መንፈሳዊያን"

በማለት ይገልጻቸዋል። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምተው በመንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋቸውን ፈቃድ በመስቀል ላይ የሰቀሉ፣ ለጌታ ለመኖር ራሳቸውን የሰጡ ናቸው። ይህም ሲባል አለቅጥ ተጋንኖ ያለ ኃጢአት የነበሩ ተብሎ ማጕላመስና መተርጐምም አግባብ አይመስለኝም፤ የእነዚህ ሰዎች ዓይነተኝነት፣ እንደ እግዚአብሔር ፍላጎትና ፈቃድ ለመኖር በመወሰን፣ በመንፈስም ለመመራት ራሳቸውን መስጠታቸው ነው። እንደዚሁም የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ለማዳመጥና እንደ ፈቃዱም ለመኖር የሚተጉና የሚታገሉ መሆናቸው ነው።

በነዚህ ዓይነት የእድገት ደረጃ ላይ የሚመደቡ አባላት ያሏት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ፣ በመሃላቸው ኃጢአት እንደ ነበረም እንረዳለን። በዚያ ጉባኤ ውስጥ ዓበይት ሆነው የሚታዩ 12 ዓይነት ኃጢአቶች እንደ ነበሩ ከመጽሐፉ መረዳት እንችላለን።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በዓቢይ ኃጢአትነት ከተቆጠሩት መሃል አንዱ መከፋፈል ነበር። ሌላው ደግሞ የድፍረት ኃጢአት ነበር። ይህ የድፍረት ኃጢአት በሥጋቸው በመመራት የሚያሳዩት መተላለፍ ነበር። በተጨማሪም የተሰጣቸውን የጸጋ ስጦታ ለራሳቸው መመኪያና መታበያ መኩራሪያ አድርገውት ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ሕብረት፣ በመሃላቸውም ያለውን አንድነት ይጠብቁ ዘንድ በመታሰቢያነት የሰጣቸውን የገበታ ትዕዛዝ፣ በራሳቸው ፈቃድና ፍላጎት በመመራት፣ መሳከሪያና መፈንጠዣ በማድረግ የጌታን ማዕድ ያረክሱ ነበር። መታየት የሌለበትና የማያስፈልገው የልጅነት ጠባይ በመሃላቸው ይታይ ነበር። መከፋፈላቸው ሥጋዊያን ከመሆናቸው የተነሳ ያመጡት ድካም እንደ ሆነም አብሮ ሐዋርያው ይጠቁማቸዋል። “ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናት ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?” (1ቆሮ. 3:3)

እነዚህን ድክመቶቻቸውንና፣ መነሻዎቻቸውንም ጭምር በሚገባ



ካስገነዘባቸው በኋላ ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ስላላቸው የጸጋ ስጦታ ዘርዘር ያለ ትምህርት ሲሰጣቸው እንመለከታለን። የትምህርቱ ማእከላዊ ጭብጥ (መግለጫ)፣ እያንዳንዱ ሰው እንደ እግዚአብሔር ጸጋ መጠን ሥጦታን ታድሏል፤ ያ ማለት ሁሉም ባለው ስጦታ በሥጋ ትምክህት ተሞልቶ ይታበይበት ማለት ሳይሆን፣ ሁሉም ስጦታውን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጎ እርሱን ያገለግልበት ዘንድ ማስፈለጉን የሚያስገነዝብ ነው። የተለያዩ ብልቶች የአንድ አካል ብልቶች እንደ መሆናቸውና አንድን አካል እንደሚያገለግሉ ሁሉ፤ አባላትም ራሳቸውን እንደ አንድ የክርስቶስ አካል በመቁጠር አካል ለሆነው ለክርስቶስ በአንድነት ማገልገል እንዳለባቸው አጽንኦት በመስጠት ያስተምራቸዋል።

ይህንን ሁሉ ካስገነዘባቸውና፣ እያንዳንዳቸው በጌታ ቸርነት መጠን በስጦታ መባረካቸውን ካበሰረላቸው በኋላ በመሃል አንድ ትልቅ ቁም ነገር ያስተምራቸው ዘንድ ቆም ይላል። ጉዞአቸውን ለአፍታ በመግታት እርሱ ለሚያሳያቸው ትልቅ መገለጥ አስተውሎታቸውን ይጠይቃል። በቆሮ. 12:32 ላይ ጠበቅ አድርጎ “ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ” በማለት ከሁሉ ወደሚበልጠው ዓላማ ሲያመለክታቸው እናያለን። “ደግሞም ከሁሉም የሚበልጠውን መንገድ ላሳያችሁ” በማለት የነበሩበትን አቅጣጫ ዞር ብለው በመመዘን መንገዳቸውን እንዲሰልሉና እንዲያስተካክሉ ይመክራቸዋል። ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በአገልግሎቱ ለማደግ ውሳኔ ላደረገ አገልጋይም ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

ከሁሉም የሚበልጠው መንገድ የፍቅር ሕይወት ነው። ከጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ይልቃል፣ ትንቢትን ከመናገር ይበልጣል፣ ከፈውስ ስጦታም እጅግ በጣም ይሻላል፤ ከአስተማሪነትም ይበልጣል፣ ከሌላም ከማንኛውም ስጦታ ይልቅ የሚበልጠው የፍቅር ሕይወት ነው። በመሠረቱ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ጥልቅ የሆነ መገለጡን ሲገልጽልን፣ በአጠቃላይ የጸጋ ስጦታ አያስፈልግም በማለት ሊያናንቅና ሊያተንስ ፈልጐ አይደለም፤

እርሱም አላለውም። እነዚህ ስጦታዎች በተገቢነታቸው የሚያስፈልጉ የቤተ ክርስቲያን ፈርጦችና ጌጦች ናቸው። ነገር ግን ዋናው ዓላማው ከነዚህ ሁሉ በላይ ደምቆና አብርቶ መታየት ያለበትን ነገር ሊያመለክት ስለሚፈልግ ነው። ስጦታዎችን በተመለከተ ጊዜ ወስዶ፣ እንዴትና ለምን መጠቀም እንዳለባቸው በትንታኔ ማስረዳቱ፣ የስጦታዎችን አስፈላጊነት ትኩረት ላለመንፈግ ነው። በእርሱ አቀራረብ በስጦታውና በአጠቃቀሙ መሃል ሊያስገባው የፈለገው ነገር አለ። በ1 ቆሮ. 12 ላይ የጸጋ ስጦታዎችን በዝርዝር ያስቀምጣል፤ 13ኛውን ምዕራፍ ዘሎ በ14ኛው ላይ የጸጋ ስጦታ አጠቃቀማቸውን በዝርዝር ሲያስረዳ እንመለከታለን። በእነዚህ በሁለቱ እውነታዎች መሃል አንዱን ከአንዱ እንደ ሰንሰለት (ሊያያይዝ) ሊያሰናስል የሚችለውን ነገር "ላሳያችሁ" በማለት ይገልጽላቸዋል። ይህ አሰናሳይ፣ አያያዥና አገናኝ የሆነው ዋነኛ ነገር ፍቅር ነው።

የአገልግሎት መሠረት ፍቅር ነው። የኑሮ መሠረት ፍቅር ነው። ከእግዚአብሕር ጋር ላለን አንድነት መሠረቱ ፍቅር ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነት የሰጠን በፍቅር ምክንያት ነው። ለአገልግሎት የሚሆነውን የጸጋ ስጦታ እንኳ የሚሰጠን ከፍቅሩ የተነሳ ነው። ስለ ፍቅር ይህን ያህል እንደ መግቢያ ከተመለከትን፣ በሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ ፍቅርን በተመለከተ የሚገኘውን እውነት በአራት ነጥቦች ከፋፍለን መረዳት እንችላለን።

የሚበልጠውን ነገር ለማግኘትና ለማደግ አገልጋይ ሊኖረው የሚገባው መሠረት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚከተሉትን እንመልከት።

## የእግዚአብሔርን ፍቅር ምንነት መረዳት።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ምንነት መረዳት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። በአገልግሎታችንና በኑሮአችን ውስጥ ሊበልጥና ትልቅ ስፍራ



ሊይዝ የምንፈልገውን ይህንን ፍቅር አስቀድመን ምንነቱን መረዳት ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ፍቅር በከፍተኛ የንጽጽር ዘይቤ በመግለጥ ያስቀመጠው በ1ቆሮ. 13 ላይ ነው። በአገልግሎታችን ውስጥ የምናስተላልፈው ጸጋ የእግዚአብሔርን ፍቅር ነው። እግረ መንገዳችንም ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ምንነት ሊያስረዱ የሚችሉ 14 ዝርዝር ነጥቦችን ማጤን እንችላለን። እነዚህ ነጥቦች በአገልግሎትና በኑሮአችን ውስጥ ያላቸው አስፈላጊነት፣ የፍቅርንም አስፈላጊነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዝርዝር የሚገልጹ ናቸው።

### 1▶ የእግዚአብሔር ፍቅር ነፃ የሚያወጣ ፍቅር ነው።

ማንኛችንም ብንሆን አገልግሎት ከመስጠታችን በፊት ነፃ መውጣት አለብን። ለዚህም ነፃ መውጣት መፍትሔ የሚሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ልባችን በሚመጣበት ወቅት ነው። ዘዳ. 4:37 እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለዘመናት ከነበሩበት ባርነት ነፃ ሲያወጣቸው፣ ምክንያቱን የገለጸው "እኔ ስለወደድኳችሁ ነፃ አወጣሁዋችሁ" በማለት ነው። ፍቅር ነፃ ያወጣል። ፍቅር አርነትን የሚሰጥ ኃይል ነው። ያለ ነፃነት ለእግዚአብሔር መኖር አይቻልም፤ ያለ ነፃነት ማገልገል አይቻልም። ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጠው ነፃነት ከሆነ ዘንዳ፣ ነፃነት ደግሞ የሚመጣው በእግዚአብሔር ፍቅር ነው። መለወጥ የሚገኘውና መፈታት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር የተገለጸው ጌታ ኢየሱስ በተሰቀለበት መስቀል ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ይለውጣል እንጂ አያሻሽልም። ያሳድጋል እንጂ ባለንበት እንድንሄድ አያደርገንም። ስለዚህ ነው እውነተኛ የአገልግሎት እድገት በፍቅር ማደግ ነው የምንለው።

### 2▶ የእግዚአብሔር ፍቅር ያድናል።

የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኔነት ያድናል፣ ከጥፋት ያድናል፣ ከዓለምና ከዓለማዊነት ያድናል፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ ያድናል። (ዘዳ.

7:7-8፤ የሐ. 3:16)

3➤ የእግዚአብሔር ፍቅር በረከትን ይሰጣል።

የጠፋውንም በረከት ይመልሳል፤ ሕይወትን ያሬሰርሳል፤ (ዘዳ. 7:13) የእግዚአብሔር ፍቅር ውስጣችንን ዘልቆ ሲገባ እንባረካለን፣ ለበረከትም እንሆናለን። በዚህ መልኩ የአገልግሎት ዕድገት በረከቱን እየተቀበልን በፍቅር እየጨመርን በሁሉም ማስተላለፍ ነው።

4➤ የእግዚአብሔር ፍቅር የእርሱ ያደርገናል።

የእርሱ ፍቅር የሚስብ ፍቅር እንጂ የሚገፋና የሚገፈትር ፍቅር አይደለም። የእርሱ ፍቅር ወደ ራሱ ያቀርበናል ያስጠጋናልም። በእርሱ ጉያ ውስጥ እንድንሆን፣ በእቅፉም እንድንኖር ያደርገናል። በጌታ እቅፍ ውስጥ መሆን ዘለቄታ ላለው የአገልግሎት እድገት ምትክ የሌለው አስፈላጊ ነገር ነው። በሥጋቸው ምሪት የተነሳ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ማገልገል በሚል መፈክር ከእርሱ ጉያ የሚርቁ ሰዎች የእግዚአብሔር ፍቅር በእርግጥ ገብቷቸዋል፣ ውስጣቸውንም ዘልቆ ተሰምቶአቸዋል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። የእግዚአብሔር ፍቅር የገባው ሰው ከእርሱ አይሸሽም። ዛሬም ቢሆን የእኛ ልመና መሆን የሚገባው ጌታ ሆይ ፍቅርህ ይገባኝ ዘንድ እርዳኝ የሚለው መሆን አለበት። (ዘዳ. 9:29)

5➤ የእግዚአብሔር ፍቅር መርገምን ወደ በረከት ይለውጣል።

ይህንን እውነት በእስራኤላውያን ሕይወት በተደጋጋሚ ሲፈጸም እንመለከታለን። ነቢዩ በለዐም በገንዘብ ተሸንግሎ እስራኤላውያንን ይረግም ዘንድ አፉን በከፈተ ጊዜ፣ ጌታ እንደበቱን ለወጠው፣ ለመርገም የተዘጋጀ ልሳን በረከትና ምርቃትን ያዥጎደጉድ ጀመር። እግዚአብሔር ልጆቹን ከማናቸውም መርገም የሚጠብቅ መከታ ነው። (ዘዳ. 23:5) ከዚህም በላይ የአገልጋዩን እንደበት በረከት ይሞላል።



6➤ የእግዚአብሔር ፍቅር ያስተምራል።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደ ወደዳቸው ከፍቅሩም የተነሳ እንዳስተማራቸው ቃሉ ይመሰክራል። በዕድገት ጉዞ ላይ ሆኖ መማር ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው የምናልፍበት ጽኑና አስተማማኝ እርምጃ ነው።

7➤ የእግዚአብሔር ፍቅር ይጠብቃል። (ዘዳ. 33:6)

በእርሱ የተወደደ በእርሱ ተማምኖ ይኖራል፣ በትከሻው መሃከል ያድራል ሲል ጌታ ከፍቅሩ የተነሳ የሚጠብቅ፣ የሚሸከምና የሚንከባከብ መሆኑን ሲያስገነዝብ ነው። የአገልግሎት ዕድገት መደላደልን ይጠይቃል። (1ቆሮ. 15:58) በጌታ ተደላድሎ ያልቆመ አገልጋይ እንደሚጠበቅበት ማደግ አይሆንለትም።

8➤ የእግዚአብሔር ፍቅር ለአገልግሎት ሥልጣንን ይሰጣል። (ነህ. 13:26)

ለምንም ዓይነት አገልግሎት ብንጠራ በብቃታችን ሳይሆን የተሾምነው፣ ከፍቅሩ የተነሳ መሆኑን በሚገባ አምነን መቀበል አለብን። ይህ ዕድገትን ከማፍጠኑም በላይ የተሰጠን መንፈሳዊ ስልጣን በአግባብ እንድንገለገልበት ይረዳናል።

9➤ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁልጊዜ እንደ መልካም እረኛ ወደ እርሱ ይመልሰናል።

ስንሸሽም ተከትሎ ይመልሰናል። ስንጠፋም ተከትሎ ያገኘናል። "በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው፤..." ይላል። (ሆሴ. 11:4) የሚያባብል ፍቅር ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ እንኳን ማደግና በአገልግሎትም ውስጥ መቆየት የሚችል ሰው አይኖርም።

### 10▸ የእግዚአብሔር ፍቅር ጸጥታን የሚሰጥ ፍቅር ነው።

ሕይወታችሁ በመታወክና በመጨነቅ ሲሞላ እግዚአብሔርን ከምንም ይልቅ ፍቅሩ ውስጣችሁን ዘልቆ ይገባ ዘንድ ጠይቁት። “አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃያል ነው፤ በደስታ በአንቺ ደስ ይለዋል፣ በፍቅሩም ያርፋል፣ በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል ይባላል።” (ሶፎ. 3:17) የእግዚአብሔር ፍቅር በሰላምና በጸጥታ ተንከባክቦ የሚያሳርፍ ፍቅር ነው።

### 11▸ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው።

የማይለዋወጥ ፍቅር ነው። “እግዚአብሔር በሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ:- በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤...” (ኤር. 31:3)

### 12▸ የእግዚአብሔር ፍቅር የማያሳፍር ፍቅር ነው።

ውስጥን የሚለውጥ፣ የነበረውን እንዳልነበረ አድርጎ የሚቀይር፣ አምላክ ስለሆነ የሚታፈርበት ፍቅር አይደለም። “...በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።” (ሮሜ 5:5) የእግዚአብሔር ፍቅር ላይን ሳይሆን ውስጥን የሚያጸዳ፣ የሚያጠራና ለክብሩ የሚያቆም ስለሆነ አያሳፍርም።

### 13▸ የእግዚአብሔር ፍቅር ወሰን የሌለው ፍቅር ነው።

“...በመንፈሱ ውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፣ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፣ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣” (ኤፌ. 3:17-19) ወደ እግዚአብሔር ሙላት ድንበርና ወሰን ሳያግደን የምንገባው በፍቅር ነው።



### 14 የእግዚአብሔር ፍቅር ጸንቶ የሚኖር ፍቅር ነው።

ይህ ፍቅር በምንም ነገር በኩል ቢያልፍ አይናወጥም። ከምንም ነገር የበረታ በመሆኑ ሊጠፋ አይችልም፤ ከመከራ፣ ከሞትና ከስቃይ በላይ ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁሉን አሸንፎ ይኖራል። ስለዚህ ነው ይህን የተረዳ አገልጋይ “ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ።” (ሮሜ 8:38-39) የሚለው።

በዚህ መልክ የእግዚአብሔርን ፍቅር ተረድተን፣ በውስጣችንም ዘልቆ ከገባ፣ አገልግሎታችን የታይታና፣ ውጭያዊ መሆኑ ይቀርና፣ ሕይወት የሚሰጥ፣ በረከት የሚሆን፣ ነፃ የሚያወጣ ይሆናል። የእግዚአብሔር ፍቅር ውስጣችንን ሲሞላ ጩኸት እንቀንስና በተግባራችን እንጨምራለን፣ እናድጋለንም። ጩኸት የሚያበዛ ባዶ ዕቃ ነው። ድምፁ ርቆ የማይሰማ ግን የሞላ ዕቃ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ “ፍቅር ግን ከሌለኝ፣ እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኛለሁ” በማለት የሚገልጸው።

## የፍቅርን ሕይወት መኖር"

ለመሆኑ የፍቅርን ሕይወት ለመኖር ፍቅር ምን ይመስላል? “ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም አይታበይም፤ ...” (1ቆሮ. 13:4) በእግዚአብሔር ፍቅር ስንሞላ በእርሱ ባሕርያት እንሞላለን፣ የቀድሞ ዓለማዊና ሥጋዊ ባሕርያችን ከውስጣችን ለቀው ይሄዳሉ። በዚህ ወቅት ተፈጥሮአዊ ሰው በደመ ነፍስ እንደሚያደርገው ለሚወዱን ብቻ አይደለም ቸርነትን፣ ምህረትንና የመሳሰሉትን የምናደርገው። ለማይወዱንም ጭምር እናደርጋለን። ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስለ ተባርኩ፣ እንቀናም፣ በእግዚአብሔር ፍቅር

ስለ ተሞላን በሌሎች መባረክ ነፍሳችን ሃሴት ታደርጋለች። ቅናት የእግዚአብሔር ፍቅር ከውስጣችን ሲጠፋ የሚታይ ምልክት ነው። ቅንነትና ፍቅር ባለበት ቅናት መኖር አይችልም። ፍቅር ሕይወትን ያፋፋል ያሳድጋል፣ ቅናት ግን መንፈሳዊ ሕይወትን ያጫጫል፣ ያመነምናል። በአገልግሎት ለማደግም እንቅፋት ይሆናል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከሁሉ የሚበልጠው መንገድ መጮህ፣ ማገልገል፣ ወዲያ ወዲህ ማለት ሳይሆን በፍቅር ተሞልታችሁ የፍቅርን ሕይወት መኖራችሁ ነው በማለት የሚመክረው። ፍቅር ካላችሁ የጸጋ ስጦታ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር በውስጣችሁ ይኖራልና፣ እግዚአብሔር በድንቅ ይጠቀምባችኋል። ፈቃዱንም በሕይወታችሁ ውስጥ ያደርጋል። ጌታ ኢየሱስም በዮሐ. 13:35 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ሲመክራቸው፤ "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፣ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።" ሲል ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር አይደለም፣ ነገር ግን ያንን የእግዚአብሔርን ፍቅር እርስ በርሳቸው በቅንነት ሲገላለጹ፣ ለጠፉትም ነፍሳት ሲገልጹ፣ ያኔ የክርስቶስ ለመሆናቸው ምልክት ታይቶባቸዋልና ለማንም ሰው በዚያ ምልክት ይታወቃሉ ማለት ነው። ይህ መለኮታዊ ምክር ዛሬ በእኛ ላይም ያለው እውነተኝነቱ ሳይለወጥ ይኖራል። አለበለዚያ እግዚአብሔርን እወዳለሁ፣ ግን ወንድሜን አልወድም ብንል፣ በእግዚአብሔር ፊት ውሸተኞች ሆነን እንገኛለን፣ እርሱም አይቀበለንም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታችን እንዴ ከፈሰሰ መገደብ ስለማይቻል እንደ ወንዝ እየተንዶለዶለ፣ ወደ ወንድሞቻችንና ወደ እህቶቻችን ዘንድ ይደርሳል። እግዚአብሔርን ከወደድን በአካባቢያችን የሚገኙትንም እንወዳለን። "አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ።" (ዮሐ. 15:9) የእግዚአብሔር ታላቁ ትእዛዝ በፍቅሩ መኖር ነው። በፍቅሩ ሳንኖር ፍቅሩን ብንዘምርና ብንሰብክ ከግብዝነት የተለየ አገልግሎት እንዳልሰጠን ማወቅ ይገባናል። የአገልጋይ እድገትና፣ የአገልግሎቱ ጥራትና ውበቱ በጌታ ፍቅር መኖሩ ነው።



# የፍቅር እንቅፋቶችን ማስወገድ።

በሕይወታችን፣ በአገልግሎታችንና በኑሮአችን ለፍቅር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች አይጠፉም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 13:8-12 ላይ ስለ እነዚህ መሰናክያዎች ይገልጻል። በመልእክቱ ላይ በተዘረዘረው መሠረት መወገድ ያለባቸውን እንቅፋቶች ነቅሰን ማውጣት እንችላለን።

## 1▸ የመበላለጥ ሕይወትን ማስወገድ።

ይህ እንቅፋት ካልተወገደ፣ ፍቅርን ከውስጣችን ይገድላል። የልጅነትን ሕይወት አስወግዱ በማለት ሐዋርያው ሲገልጽ፣ ከልጅነት ባሕርያት አንዱ መበላለጥ ላይ ትልቅ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው። ስለዚህ ይህ ሕይወት ደግሞ የፍቅር መቅሰፍት ነው። ጠላት በዚህ ዘመን ከክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ፍቅርን ለመግደል የሚጠቀምበት ትልቁ ዘዴ ይህንን የመበላለጥ ሕይወት በውስጣቸው በስውር በመዝራት ነው። ታዲያ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ልብ ብለው የነቁበት አይመስልም። የመበላለጥ ሕይወት እስካለ ድረስ የቅናት ሕይወት አለ፣ የቅናት ሕይወት እስካለ ድረስ ወንድሜንና እህቴን ማየት አልሻም፣ በእነዚህ የእንቅፋት ሰንሰለቶች ተሰነካክዬ እንድወድቅ ሰይጣን ጥርጊያ ጎዳናን የሚያበጀው የመበላለጥ መንፈስ በውስጤ በመዝራት ነው። በጸጋ ስጦታ እንኳ ለመበላለጥ ደፋ ደፋ ያልንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም።

## 2▸ የውድድር ሕይወት።

እንደ እከሌ አለዚያም ከእከሌ በላይ ሆኜ መገኘት አለብኝ የሚለውን እንቅፋት ይመለከታል። ሐዋርያው ጳውሎስ "አክሊልህን ማንም እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ" ብሎ ሲመክር፣ ዛሬ ደግሞ ያ ሕይወት ሊተረጐም የተሞከረው ያለ አግባብ ነው። ይኸውም ብዙዎቹ አክሊላቸውን ሳይሆን፣ ያላቸውን ማዕረግ፣ ሥልጣን፣ ገንዘብ የመሳሰሉትን

ነው ሙጭጭ ብለው ይዘው የሚገኙት። በምታደርገው ነገር ሁሉ ማንም እንዳይደርስብህ የተባለ ይመስል ሁሉም በየፊናው ቀድሞ ሲሮጥ ነው የሚታየው። ይህ የውድድርን ሕይወት ነው አጉልቶ የሚያሳየው። የውድድር ሕይወት ያደክማል፣ አያዝናናም ያስጨንቃልም።

### 3▶ የአትንካኝ ሕይወት።

ይህም የልጅነት ሕይወት ነጸብራቅ ነው። ክርስቲያኖች አብረው ሳያገለግሉ፣ ሳይደሰቱ፣ አብረው በአምላካቸው ሐሴት ሳያደርጉ አትንካኝ በመባባል ብቻ ዘመናቸውን ሲገፉ ማየት ለእግዚአብሔር ምንኛ ኃዘን ነው! አትንካኝ የሚለው ስሜት ብዙን ጊዜ የሚመጣው ከመናናቅ ነው። "ማን ነህና ልትነካኝ" የሚለው የዕብሪት ስሜት የሚፈልቀው ንቀት በልብ ውስጥ ስር ሰዶ ሲንሰራፋ ነው።

### 4▶ የመኵራረፍ ሕይወት።

አትንካኝ የሚለው ስሜት የሚመጣው ከመኵራረፍ በኋላ ነው። ልጆች በትንሹ ኩፍ ማለት ይቀናቸዋል። ሰዎችም የልጅነት ጠባይ እስካልለቀቃቸው ድረስ በትንሹ ነገር ኩርፊያቸው ይበዛል። ያ ኩርፊያቸው ለብስጭት ይዳርጋቸዋል። ኩርፊያ ልብን ተራራ ካሳከለ ንቀትንም በውስጣችን ያሰርጻል። ማበጥ ባለበት መገፋፋት አለ። ፊኛ ሲነፋ ቦታ አይበቃውም ሌላውንም የመግፋት ባሕርይ ይታይበታል። ኩርፊያ እንደ ፊኛ መነፋት ማለት ነው።

### 5▶ የልጅ ንግግር።

ልጆች አስበውና አስተውለው አይናገሩም፣ ስሜታዊያን በመሆናቸው የመሰላቸውን ይናገራሉ። የበሰለ ንግግር አያውቁም። ያንጻል፣ ይጠቅማል፣ በሽተኛ ነው፣ ጤነኛ ነው ብለው መዝነው አይናገሩም። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ



የሚያሳዝነውን ነገር፣ እንደ ልጆች በስሜት በመነዳት ሳናስተውል የምንናገረው ንግግር ነው። መገንባቱንና ማፍረሱን፣ ሕይወት መስጠቱንና መግደሉን ሳንገመግም እንደ መጣልን ብቻ የምንናገረው ንግግር ጌታችንን ያሳዝነዋል። ይህም ለእግዚአብሔር ፍቅር ትልቅ እንቅፋት ነው።

### 6▶ የልጅ አስተሳሰብ።

ልጆች ሃሳባቸው የጸና አይደለም። አንድ ወጥ የሆነ መልክ የለውም፣ በየጊዜው ይቀያየራል። ልጆች እቅድ የላቸውምና፣ ሃሳባቸውም በዓላማ የተመራ አይደለም። ብዙ ጊዜ ሃሳባቸው በውጥን መቅረቱን የምንመለከተው፣ የጀመሩትን ሳይጨርሱ ተሰላችተው ወደ ሌላው ነገር ሲገቡ ነው። ልጆች ስለሆኑ ሃሳባቸውም የረጋና የሚታገስ አይደለም። ልጆች ቃላቸውን መጠበቅ ይከብዳቸዋል። አንድም ይረሱታል፣ አለዚያም ቃላቸውን ይጠብቁ ዘንድ ሁኔታው ያሳሳቸዋል። ስለዚህ ቃላቸውን ለመጠበቅ ይቸገራሉ። በብዙ ቦታ በአያሌ ክርስቲያኖች ላይ የሚታየው ባሕርይ ከዚህ የተለየ አይሆንም። ሰዎች ቶሎ ብለው ከጌታ ጋር ቃል ይገባሉ፣ አፈጻጸሙ ላይ ግን ወይም ዘንግተውታል አለዚያም ለመፈጸም ሲያቅታቸው ይታያሉ። ይህ ዓይነቱ የልጅነት ጠባይ የገነነበት አስተሳሰብና እርምጃ ለአገልግሎት እድገት ትልቅ እንቅፋት ነው።

### 7▶ ውለታን መቁጠር።

ፍቅርን ከሚያጠፉ ከልጅነት ጠባዮች አንዱ ውለታን መቁጠር ነው። ትናንት፣ ዓምና፣ ካቻምና እንዲህ አድርጌ አልነበረምን? በማለት የውለታን ዜና መዋዕል ማነብነብ የልጆች ጠባይ ስለሆነ ፍቅርን ያጠፋል። እኔ እንዲህ አድርጌልሃለሁ ዛሬ አንተ ለእኔ ተገዥ መሆን አለብህ በማለት በውለታ ተጽእኖ ሌላውን ለመጫን መሞከር ፍቅርን ያሻክራል። የሰው ሕይወት በገንዘብና በቁሳቁሳዊ ነገሮች ይገዛ ዘንድ የጌታ ፈቃዱ አይደለም። "እልአዛርን ፍቱትና ይሂድ" ነው ያለው። የሰው ሕይወት

ከሰው ትብታብ ነጻ መሆን አለበት። ውለታን መቁጠር የሚያበዛ ሰው ፍቅርን መግለጽ አይችልም። የሚያደርገው ሁሉ በጥርጥር የሚመለከቱት እንጂ ከፍቅር እንዳደረገው ሁሉ ተቀባይነት የለውም። ሰው ያደረገውንም ሁሉ በዋጋ ስለሚተምን በውስጡ ፍቅርን ማዳበር አይችልም። የእግዚአብሔር ፍቅር ቀንበር "በነፃ እንደተሰጣችሁ በነፃ ስጡ" የሚል ነው።

### 8▸ ምክንያት መስጠት።

ለምናደርጋቸውና ለሚታዩብን ድክመቶች ሁሉ እንደ ልጆች ምክንያት ለመስጠት መጣደፍ ማለት ነው። ምክንያቶቹ ሁሉ የልጅነት ስለሆነ እግዚአብሔርን አያረካውም፣ ያሳዝነዋል። በዚህ ምክንያት በውስጣችን ሊኖር የሚገባውን ፍቅር ያጠፋዋል።

### 9▸ አቅምን አለማወቅ።

ልጆች ብዙ ጊዜ አቅማቸውን ገምተው አያደርጉም። እኛም ዛሬ በአገልግሎታችን ውስጥ ያለ አቅማችን ገብተን የዳከርንበትና ብዙ ነገር ያበላሸንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም።

### 10▸ ጊዜያዊውን ነገር በዘላለማዊው ለመተካት መሞከር።

በጊዜያዊ ነገር መታለል የልጅነት ጠባይ ነው። ጊዜያዊ ነገር ብልጭልጭ ስለ ሆነ ይማርካል። ክርስቲያኖችም መስለው በመቅረብ በብልጭልጭም ነገሮች በመታለል፣ ዘላለማዊውን ነገር የምንጥልበት ጊዜ ትንሽ አይደለም።

### 11▸ ስልቹነት።

አንዳንድ ነገር ጀምሮ ዳር ያለማድረስና ስልቹነት የልጅነት ጠባይ ነው። ዘማሪ ሆኖ በዚያ ሳይቀጥሉ ማቋረጥና ወደ ሌላው የአገልግሎት ዘርፍ መግባት፣ በዚያም ተሰላችተው ወደ ሌላው መግባት ያ



ነው ስልቹነት የተሰኘው የልጅነት ጠባይ። ከእግዚአብሔር የሆነውን ለይቶ ከዚያ ጋር በመቆራኘት ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ያለ መሆን፣ የልጅነት ጠባይ ነው። ዋጋ የሚከፍሉ ያደጉ ሰዎች ናቸው።

## መጽናት የሚገባውን ማጽናት"

"እንዲህም ከሆነ፡- እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።" (1ቆሮ. 13:13) መጽናት የሚገባው ምን እንደሆነ ተገልጧል ይኸውም ፍቅር ነው። ሌላው ቢያመልጠን ፍቅር ግን ሊያመልጠን ስለማይገባ፣ እርሱን መከታተል ይኖርብናል በማለት ነው ሐዋርያው የሚመክረው። ሊጸኑ የሚገባቸው ነገሮች እምነት፣ ተስፋ ፍቅር ናቸው። እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው። ምንም ነገር ብንተው ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት አጽንተን መያዝ ይኖርብናል።

ተስፋ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን አካሄድ ነው። ክርስቲያን ያለ ተስፋ ጉዞውን መቀጠል አይችልም።

ፍቅር በእግዚአብሔር ውስጥ ያለን ሕይወት ነው። ፍቅር ለዘላለም ይጸናል የሚለው ለዚህም ነው። ሁኔታዎች ይለወጡ ይሆናል በእግዚአብሔር ውስጥ ያለን ሕይወት ግን በዘላለማዊነቱ ጸንቶ ይኖራል።

ከሁሉ የሚበልጠው በእግዚአብሔር ውስጥ ያለን ሕይወት ነው፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።

# ምዕራፍ ስድስት
# እግዚአብሔርን መውደድ





## ም ዕ ራ ፍ  ስ ድ ስ ት

## እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ን  መ ው ደ ድ

“እርሱም መልሶ፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደደው፣ ባልጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው።” (ሉቃ. 10:27) ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ጸጋ ስጦታ ማወቅ የሚገባቸውን ከነገራቸው በኋላ፣ እንግዲህ ከሁሉም የሚበልጥ መንገድ ላሳያችሁ በማለት ልባቸውን ሰፋ አድርገው እንዲከታተሉ ያሳስባቸዋል። ያም እንግዲህ ሊያሳያቸው የፈለገው ከሁሉም የሚልቀውን ጉዳና፣ የፍቅር ጉዳና ነው። ከአገልግሎታችሁ በፊት ቅድሚያ ልትሰጡት የሚገባው ነገር ፍቅር ነው በማለት ያሳስባቸዋል።

ከሁሉም የሚበልጠው መንገድ፣ እግዚአብሔር አምላካችንን በፍጹም ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አሳባችንና መንፈሳችን መውደድ ነው። እግዚአብሔርን በቅድሚያ መወደድ የሚገባው ስለምንም ነገር ሳይሆን፣ ስለ ማንነቱ ነው። ከእግዚአብሔር በልጠ ሊወደድ የሚገባው ምንም ዓይነት ፍጥረት አይኖርም። የእግዚአብሔርን እውነት፣ ንጽህና፣ ቅድስና፣ ጥንቃቄ፣ ምህረትና ርኅራኄ ስናይ ከዚያ የበለጠ ይወደድ ዘንድ ሥፍራ ልንሰጠው የሚገባ ምንም ነገር አይኖርም። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚያም የተሻለ ነገር መርጣችሁ ውደዱ የሚለው። እንግዲህ ከእግዚአብሔር የተሻለ ነገር ምንም እስከሌለ ድረስ የፍቅራችን ዕጣ የሚወድቀው በእግዚአብሔር ላይ ነው።

እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱ መውደድ ስንጀምር ውለታውንም አብረን መረዳት እንጀምራለን። የእግዚአብሔርን ውለታ ባስተዋልንና በተረዳን ቁጥር፣ በእርሱ ፍቅር በእውነት በፊቱ እንንበረከካለን። ለዚህም ነው

ሐዋርያው ዮሐንስ "እርሱም አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።" (1ኛ ዮሐ. 4:19) በማለት የገለጸው። ጳውሎስም ከዚሁ እውነት በመነሳት ቅዱሳንን "እግዚአብሔርን ውደዱት" በማለት ያደፋፍራል። የእርሱንም አገልግሎት ምክንያትና ብርታቱንም የእግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ለማስረዳት "የእግዚአብሔር ፍቅር ግድ ይለናልና" ይላል። (2ቆሮ. 5:14) ጴጥሮስ በበኩሉ እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ በማለት በፍቅር በተመሠረተ ሁኔታ በቃሉ ለማደግ ጥረት እንዲያደርጉ ቅዱሳንን ያሳስባል። አዎ። የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ ፍቅር ርኅራኄውንና ምህረቱን አይቶ ወደ ኋላ የሚል ሰው ሊኖር አይችልም። (ሮሜ 8:35-39)

እንግዲህ እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ መውደድ እንደሚገባን ከተረዳን ዘንዳ፣ እግረ መንገዳችንንም እርሱን የምንወድበትን ሦስት ዓይነት የፍቅር መንገዶች እንዳሉን ጠለቅ ብለን ባንገባበትም ላይ ላዩን መመልከት ሳይጠቅመን አይቀርም።

## እግዚአብሔርን ለጥቅም መውደድ

የመጀመሪያው እግዚአብሔርን የመውደድ ዓይነት እግዚአብሔርን ለራሳችን ስንል ስንወድ ነው። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን በማንነቱ ሳይሆን፣ ከእርሱ ለሚያገኙት ጥቅምና መብት ሲሉ ብቻ የሚወዱት እንዳሉ የታወቀ ነው። ድንበር ማበጀቱ እንኳ ባያስፈልግም ይበልጥ ሁኔታውን ግልጽ ለማድረግ፣ በተለይ በምዕራባውያንና በዚያ ባሕል ክልል ውስጥ የሚገኙ በአብዛኛው እግዚአብሔርን በማንነቱ ሳይሆን፣ ከእርሱ ለሚያገኙት ጥቅም አኳያ ሲሰጡ የእግዚአብሔር ፍቅር ግድ ብሎአቸው ሳይሆን ነገ እርሱ በእጥፍ ይመልስልናል በሚል በንግድ ስምምነት ዓይነት ነው። ይህ ጤናማ ፍቅር አይደለም። እግዚአብሔር ከእርሱ የምናገኘውን ትርፍ ብቻ ተስፋ አድርገን መውደዱ፣ ከጥላቻ ያላነሰ ጸያፍ የፍቅር መግለጫ ነው።



ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከዓለማውያን ፍቅር የሚሻልበት ምንም መንገድ የለም። ምናልባት ከጊዜ ብዛት፣ ፍቅሩን በዚህ ሁኔታ የጀመረው ግለሰብ፣ ዓለም የተሻለ ትርፍ እንደምትሰጥ በተሰማው ጊዜ እንድያውን ጠቅልሎ የተሻለ ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ይገባል። መሠረቱ ትክክል አይደለምና። ዮሐንስ "ማንም ዓለምን የሚወድ የአባት ፍቅር በውስጡ የለም" (1ዮሐ. 2:16) በማለት የገለጸው ለዚህ ነው።

እግዚአብሔርን በእውነተኛው መንገድ መውደድ ወደ ቅድስና ያመጣል። ከዚያም አልፎ ለሌላ ሰው መራራትን፣ ምህረት ማድረግን ያመጣል። ለዚህም ነው በሕጉ እንደ ተጻፈው፣ እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ ነፍስህና ኃይልህ ውደድ ካለ በኋላ፣ ከዚያ በመቀጠል ጐረቤትህን ውደድ የሚለውም ትዕዛዝ የተቀመጠው።

## እግዚአብሔርን ስለ እርሱነቱ መውደድ

ሁለተኛው የፍቅር ዓይነት ደግሞ፣ እግዚአብሔርን ስለ እርሱነቱ መውደድ ነው። እግዚአብሔርን ስለ እግዚአብሔርነቱ በምንወድበት ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰቱ ነገሮች አሉ። እነርሱም:-

1▸ ትዕዛዙን መውደድ እንጀምራለን።

እግዚአብሔር አድርግ የሚለንን ነገር እንደ በረከት እንጂ እንደ ሸክም አንቆጥረውም። ሐዋርያት የደረሰባቸውን መከራና ችግር ሁሉ እንደ ክብር የቆጠሩት እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መውደድ ምን እንደሆነ ስለ ገባቸው ነው። "እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ ከሸንጎ ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤" (ሐዋ. 5::41)

2▸ ፍቅራችን ከስሜታዊነት ዘልቆ ተግባራዊ ይሆናል።

ስሜታዊ ፍቅር እንደ ግራፍ ከፍና ዝቅ በማለት ይለዋወጣል፣ በተግባር የታቀፈ ፍቅር ግን ሕያው ሆኖ ይኖራል። ተግባራዊ ፍቅር የሚጨበጥና የሚታይ ነው። በሌላ አነጋገር በሁኔታዎች ምክንያት አይለዋወጥም። "ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም፣ ፈሳሾችም አያሰጥሙአትም።" (መ. መ. ዘሰ. 8:7)

3▸ ድምጹን መውደድ እንጀምራለን።

እርሱ ለእኛ የሚናገርበትን ጊዜ መናፈቅ እንጀምራለን። እርሱ ሲናገር ልባችን በውስጣችን ይቃጠልብናል።

4▸ የእግዚአብሔርን መንገድ መውደድ እንጀምራለን።

በመዝ. 118 ዳዊት ስለዚህ እውነት ነው በመዝሙሩ ሲያዜም የምናነበው።

5▸ እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ መባረክ እንጀምራለን።

ለዚህም ነው ዳዊት የጌታ ፍቅር ገብቶት "ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን።" (መዝ. 102:1) በማለት የተቀኘው። ሁለመናችን እግዚአብሔርን ያከብራል ይባርከማል።

6▸ የእርሱን ቤተ መቅደስ እንናፍቃለን።

በቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር ኪዳን ስላለ ያንን መናፈቅ እንጀምራለን። "እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፣ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ።" (መዝ. 26:4) ያ ፍቅሩ ከዘለቀን በኋላ በሕይወታችን ውስጥ ከሚከሰቱት ዋነኛ ነገሮች አንደኛው ነው። ጌታን መጠማትና ጌታን መናፈቅ የፍቅር መግለጫው ዋንኛው መንገድ ነው። መዝ. 62።



## ለእግዚአብሔር ክብር ብሎ ራስን መውደድ

ሦስተኛው የፍቅር ዓይነት፣ ለእግዚአብሔር ብለን ራሳችንን መውደድ ነው። ለራሳችን ብለን እግዚአብሔርን ስንወድ ማንነታችን ገሃድ የወጣ ነው። ይኸውም ትርፍን ተስፋ በማድረግ ነው። ለእግዚአብሔር ብለን ራሳችንን ብንወድ ደግሞ ራሱን የቻለ ጥልቅና አስደናቂ ትርጉም አለው። ይኸውም:- ለእግዚአብሔር ብለን ራሳችንን ስንወድ እግዚአብሔር ለማንነታችን ሲል ትልቅ ዋጋ ከፍሎበታልና፣ ልጁ በመስቀል ላይ ደሙን አፍሶበታልና፣ ታላቅ ፍቅሩንም ገልጾበታልና፣ ራሳችን ለእግዚአብሔር ውድ ስለሆነ እኛም ራሳችንን በዚህ ፍች አንጻር መውደዳችን ነው። ማንነታችን እንዳይረክስ እንጠነቀቃለን። ዓላማችን ግባችን፣ አሳባችንና፣ ፍላጐታችን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ራሳችንን ወደድን ስንል ራሳችንን ለእግዚአብሔር ቀደስን ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን ሦስት ዓይነት ሰዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲቀድሱ የተለዩ ሰዎች እናገኛለን። የመጀመሪያዎቹ ናዝራዊያን ናቸው። የስማቸውም ትርጓሜ ለእግዚአብሔር የተለየ ማለት ነው። ናዝራዊ ማድረግ የሚገባውና ማድረግ የማይገባው ነገር ተደንግጎለታል። ማድረግ ከማይገባው ነገሮች መሃል ሦስቱ፣ አንደኛ ጸጉሩን አይላጭም ነበር። ሁለተኛ ሬሳ ወይም በድን አይነካም ነበር። ሦስተኛው ደግሞ የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ነበር። ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተለየና የጌታ መንፈስ ማደሪያ ስለሆነ ራሱን በቅድስና የመጠበቅ ኃላፊነት ነበረበት። ጸጉሩ፣ ሊመጣ ያለውን የክርስቶስን ራስነት በተምሳሌነት ይወክላል። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራስ የሆነው ክርስቶስ መከበር አለበት። መነካት የለበትም። የሶምሶን ውድቀት የተከተለው የራሱን ጸጉር ካስላጨ በኋላ ነው። ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክብሩን ሲያጣ የሚከተቀው እርምጃ ውድቀትና መታወር ብቻ ነው። ሶምሶን በጊዜ ብዛት ቀስ በቀስ ጸጉሩን እንዳስላጨ፣ እኛም ዛሬ በሕይወታችን ራስ ሆኖ የሚገኘውን

የክርስቶስን ክብር የምናስወስደው "ምን አለበት" በሚለው የቀዘቀዘነት ሕይወት ተደልለን፣ በጊዜ ብዛት ተሰናክለን እንደ ሆነ ልብ ልንል ይገባናልና ከዚህ ዓይነቱ ስህተት ራሳችንን መጠበቅ ይኖርብናል።

የሚያሰክር መጠጥ ናዝራዊ የሆነ ሰው አለመጠጣቱ ኤፌሶን 5:18 "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ" የሚለውን ቃል አጽንኦት ሲሰጥና ሲወክል ነው። የአዲስ ኪዳን ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን አይኖርባቸውም። "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" (ኤፌ. 4:30)

ናዝራውያን ሬሳን አይነኩም ነበር። ሬሳ የዚህን ዓለም ሕይወት የሚወክል ተምሳሌት ነው። በኃጢአታችሁና በበደላችሁ ሙታን ነበራችሁ የሚለውም ለዚህ ነው። ናዝራዊ ሆኖ ራሱን ለአምላኩ የለየ ሰው የድሮውን ሙት የሆነውን ሕይወት ተመልሶ ይነካ ዘንድ ተመልሶ ይኖረው ዘንድ አይፈቀድለትም። በክብር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናልና። ኑሮአችን፣ አካሄዳችን፣ አነጋገራችን ሁሉ ሰማያዊ ይሆን ዘንድ ይገባዋል እንጂ፣ በክብር ከተቀመጥንበት ሥፍራ ወርደን ራሳችንን ማርከስ አይገባንም ማለት ነው። "...በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።" (ኤፌ. 2:6-7)

ናዝራዊ ራሱን ባለማርከስ ራሱን የሚጠብቀውና የሚወደው እግዚአብሔር ስለ ለየው ነው። እርሱም እግዚአብሔርን ስለሚወድ ነው። ካህናቶች ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት በሚቆሙበት ጊዜ ንጹህና ቅዱስ ሆነው መቅረብ ስላለባቸው ራሳቸውን፣ መንፈሳቸውንና ሃሳባቸውን በንጽህና ይጠብቃሉ። ራሳቸውን ይወዳሉ፤ ስለ እግዚአብሔር ሲሉ፤ አይረክሱም፣ አይነወሩም። ካህናት ልብሳቸው መጠበቅ አለበት። ይህም ፍችው ከውጭ የሚታየው ምስክርነታቸው ያለ ነቀፋና ያለ እድፍ መጠበቅ ነበረበት ማለት ነው። "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፣ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድንሆን ላደረገ፣ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።" (ራእ. 1:5-6)



ነቢያት ለእግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች ናቸው። የነቢያት ጥሪ በመንፈስ መመራት ነው። በሥጋ መሄድና መመራት አይገባቸውም፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ሲወዱ የመንፈስ ምሪትን በሚገባ ይጠብቃሉ ይታዘዛሉ። እግዚአብሔር የሚያዛቸውን ብቻ መፈጸም ሃላፊነታቸው ነው። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ብለን በምንወድበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆናችንን ከተረዳን መቅደሱን በሚገባ እንጠብቅለታለን። "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" (1ቆሮ. 6:19-20) የሚለው ቃል የታመነ ነው። ከዚያ በኋላ ነው ጌታ አምላኬን በፍጹም ልቤ በፍጹም ነፍሴ፣ በፍጹም መንፈሴ፣ በፍጹም ኃይሌ እወደዋለሁ በማለት ምስክርነታችንን መስጠት የምንችለው።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ነው እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ አገላለጽ የተሻለ፣ ከሁሉም የሚበልጥ አገልግሎት ሰጥተናል ማለት የምንችለው። እንግዲህ ይህ ከሁሉም በላይ የሆነ መተኪያ የሌለው የአገልግሎት እድገት ጉዳና እግዚአብሔርን መውደድ ነው።

# ምዕራፍ ሰባት
# እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ማወቅ








## ግ ዚ አ ብ ሔ ር ከ እ ኛ የ ሚ ፈ ል ገ ው ን ማ ወ ቅ

ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለአምላካችን ክብር ብቻ ለመኖር የምንፈልግ ከሆነ በቅድሚያ የሚለንን ለይተን ልናውቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልግብንን ማወቅ ያስፈልጋል። ሙሴም ለእስራኤል ሕዝብ ያስተላለፈው መሠረታዊ መልእክት ይህ ነበር። “እስራኤል ሆይ፣ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ፣ መንገዱንም ሁሉ ትሄድ ዘንድ፣ አምላክህንም እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፣ በፍጹምም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ፣ መልካምም እንዲሆንልህ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሥርዓት ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው?” (ዘዳ. 10:12-13) “እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው?” በማለት ነው ሙሴ እስራኤላውያንን የጠየቀው። ከሙሴ መልስ 12 ነጥቦችን በዝርዝር መመልከት እንችላለን።

1➤ እግዚአብሔርን መፍራት
2➤ በመንገዱ መሄድ
3➤ እግዚአብሔርን መውደድ
4➤ እግዚአብሔርን ማምለክ
5➤ የእግዚአብሔርን ታላቅነት መገንዘብ
6➤ የእግዚአብሔርን ውለታ ማሰብ
7➤ በንጽሕናና በቅድስና ሕይወት መኖር
8➤ እግዚአብሔርን መስማት
9➤ በእግዚአብሔር ርኅራኄ መመላለስ

10▸ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መጽናት

11▸ ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ

12▸ እግዚአብሔርን ማክበር ናቸው።

እነዚህን መሠረታዊ ባህርያት ዘርዘር አድርገን መመልከት ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል።

## 1▸ እግዚአብሔርን መፍራት።

"አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ..." (ዘዳ. 10:12) ብሎ ለእስራኤል ሕዝብ ማሳሰቢያ ይሰጣል። ማሳሰብያው ዛሬም ለእኛ ለሁላችን በእግዚአብሔር ስም ለተጠራን፣ በመንፈሱ ለታተምን፣ በጌታ ደም ለነጻን ሁሉ የሚሠራ ዘላለማዊ ማሳሰቢያ ነው። ለመሆኑ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ለእርሱ የሚገባውን መልሶ መስጠት ማለት ነው። ለእርሱ የሚገባውን መስዋእት፣ አክብሮት፣ አምልኮት፣ ጊዜ፣ በፍርሃትና በትህትና እንዲሁም በደስታ እናቀርብለታለን። ፈሪሃ እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ዙፋኑን ሲዘረጋ እነርሱም ከድፍረትና ከግድየለሽ ኃጢአት ነፃ ይወጣሉ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ቀኑን ሙሉ በግድየለሽነት አይኖርም። እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልግ ሰው በድፍረት ኃጢአት ውስጥ አይመላለስም። ዳዊትም የጸለየው ጸሎት የሚያጸናው ይህንኑ እውነት ነው። "እግዚአብሔር ሆይ ከድፍረት ኃጢአት አንጻኝ።" ያለው ፈሪሃ እግዚአብሔር ልቡን በሞላ ጊዜ ነው። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች ቅን ልብ ስላላቸው፣ እግዚአብሔርን ከነሙሉ ክብሩና ስልጣኑ ያዩታል። በዚህ ወቅት ራሳቸውን ከድፍረትና ከግድየለሽነት ኃጢአት ይጠብቃሉ፤ ይርቃሉም። እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ላይ የሚታየው እንደበታቸውን የመግዛት ሕይወት ዋነኛ ምልክታቸው ነው። ምላሳቸው አይገዛቸውም፣ እነርሱ ይገዙታል እንጂ። ምላሳቸው የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ



ይናገራል። ታላቅነቱን ያወጋል። ለዚህም ነው ሐዋርያት እኛ ግን ለጸሎትና ለቃሉ አገልግሎት እንተጋለን በማለት ያወጁት። ምክንያቱም በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደበታቸው በእግዚአብሔር እሳት ተነክቷልና። እንደበትን መግዛት ምንኛ ታላቅ ነገር ነው። ያዕቆብ አንደበቱን የሚገዛ ሰው ብርቱ ነው ብሎ ያሞካሸዋል። እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ቅን ካልሆነ ፍርድ ይለያሉ። በሚያዩትና በሚመስላቸው ብቻ ተንተርሰው አይፈርዱም እውነት የሆነውን ብቻ በመናገር ቅን ፍርድን ይፈርዳሉ። ከእውነተኛ ነገር ጋር ብቻ ይተባበራሉ። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ በጻፈው መልእክቱ ምዕራፍ 4:8 ላይ ተጽፎአል። ፈሪሃ እግዚአብሔር የነገሠበት ሰው፣ ከኩራትና ከትዕቢት በሽታ ነጻ ይሆናል። በአምላክነቱ፣ በታላቅነቱ፣ በግርማና ሞገሱ፣ በጌትነቱና በገዥነቱ አምላክን መፍራት ያ ቀዳሚ የሆነና ክርስቲያን በትጋት ሊጠብቀው የሚገባ ጉዳይ ነው።

## 2▸ በመንገዱ መሄድ።

"እስራኤል ሆይ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ፣ በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ፣..." ይላል። (ዘዳ. 10:12) እግዚአብሔርን መፍራታችን የሚታወቀውና የሚታየው በመንገዱ በመሄዳችን ነው። ታዲያ ይህ "በመንገዱ መሄድ" ማለት ምን ማለት ነው? አዎ! በመንገዱ መሄድ ማለት እንደ ቃሉ መኖር፣ ፈቃዱን ማድረግ፣ ከሌላ የከፋት መንገድ መለየት ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንገድ ከሌሎች መንገድ የተለየ ነው። "ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፣ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ።" (መዝ. 1:1) ለአምላኩ ተለይቶ ከአምላኩ ፈቃድና ጉዳና ፈቀቅ ሳይል በክፉዎች መንገድ ላይ ያልቆመና ያልሄደ ሰው ምስጉን ነው ይለዋል፤ ዘማሪው ዳዊት ይህን በማድረጉ እግዚአብሔር የሚሰጠው ዋጋ የሚለግሰውም በረከት አለ። ይህንን በረከት በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 1 ላይ በዝርዝር ሰፍሮ እናገኘዋለን።

ለክፉዎችም የተመደበውን ዕጣ በዚያው ንጽጽር ሰፍሮ እንመለከታለን። በእግዚአብሔር የጻድቃን መንገድ እንደሚታወቅና የክፉዎችም መንገድ እንደሚጠፋ በሚገባ ተገልጿል። የእግዚአብሔርን መንገድ ሰፋ አድርገን ስንመለከት 8 ነጥቦችን በዝርዝር መቀኘት እንችላለን።

2:1 በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ማለት እንደ ቃሉ መኖር ማለት ነው።

2:2 ፈቃዱን ማድረግ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ ሃሳባችን፣ ስሜታችንና ልባችን ማድረግ ማለት ነው።

2:3 እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው ነገር ራሳችንን ለይተን መስጠት ማለት ነው።

2:4 በአዲስ ሕይወት መመላለስ ማለት ነው። "እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣..." (ሮሜ. 6:4)

2:5 የእምነትን ሕይወት መኖር ማለት ነው። "እንግዲህ ሁልጊዜ ታምነን፣ በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና..." (2ቆሮ. 5:6)። በማየት ሳይሆን በእምነት መመላለስ እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኝ፣ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ማለት ነው።

2:6 በመንፈስ መመላለስ ማለት ነው። "ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።" (ገላ. 5:16) የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ማድረግ ማለት ነው።

2:7 እንደሚገባን እንደ ጥሪአችን መመላለስ ማለት ነው። "እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤" (ኤፌ. 4:1)

ክርስቲያኖች እንደ ጌታ ልጅነታቸው ሊመላለሱበት የማይገባቸው መንገድና አካሄድ አለ፤ ስለዚህም ነው የእግዚአብሔር ቃል ከዓለም እንለይ ዘንድ የሚያሳስበን።

2:8 በፍቅር መመላለስ ማለት ነው። "እንግዲህ እንደ ተወደዱ



ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፣ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።" (ኤፌ. 5:1-1) በዚህ ጥቅስ ላይ እንደ ተገለጸው በፍቅር መመላለስ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ማለት ነው።

## 3▸ እግዚአብሔር አምላክን መውደድ።

እርሱን የምንፈራ ከሆነ በእርሱ ፍርሃት ተሞልተን በመንገዱ የምንሄድ ከሆነ፣ የሚቀጥለው ውጤት እግዚአብሔርን መውደድ ነው። እግዚአብሔርን ስንወድ አንድ በድንቅ የሚከናወን አስገራሚ ነገር አለ። ይኸውም በሰብዐዊነት ሚዛን ለሚወደድ ሰው ትልቁ የፍቅር መግለጫ የከበረም ቢሆን የቀለለ ስጦታን መስጠት ነው። ከሁሉ በላይ ግን እጅግ የከበረ ስጦታ የሚሆነው ራስን በምንሰጥበት ጊዜ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔር ውዴታ በሙላት በውስጣችን ሲገባ በእኛም ሕይወት የሚፈጸመው ትልቁ እርምጃ ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን መስጠት ይሆናል። ራሳችንን ለእርሱ ሰጥተን ፍቅራችንን ለመግለጽ እንወስናለን። እግዚአብሔር ከልጆቹ የሚፈልገው ቁሳዊ ስጦታን ሳይሆን እነርሱን ራሳቸውን ነው። ስለዚህ ነው ጌታ ከአገልግሎታችን የበለጠ እኛን የሚፈልገው። በራሳችን ቦታ ስብከታችንን፣ ዝማሬአችንን፣ ሌሎችንም የጸጋ ስጦታዎቻችን መስጠቱ አግባብ አይደለም፣ እርሱንም አያረካውም። ደስ የሚያሰኘው ስጦታችን ራሳችንን ለእርሱ ስናቀርብለት ነው። ከዚያም በኋላ በተረፈው የእኛም ልብ በእግዚአብሔር ፍቅር ይሞላል፣ ሌሎችንም እንዲሁ እንድንወድ እንሆናለን።

## 4▸ እግዚአብሔርን ማምለክ።

እግዚአብሔርን ከወደድን በኋላ እኛ የራሳችን እንዳንሆን ለእርሱ

ሰጥተናልና፣ ራሳችንን መስጠታችንንም የምንገልጸው እርሱን በማምለክ ነው። እግዚአብሔርን አመልከዋለሁ ብሎ፣ ለጸሎት ጊዜ ያጣ ሰው በእውነት የጌታ ፍቅር በውስጡ አለ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። እግዚአብሔርን የምንወድድ ከሆነ እርሱን ለማምለክ መስዋዕት እንሰዋለን። ያለ ዋጋ ለአምላክ መስዋዕትን አናቀርብም። እግዚአብሔርን ለማምለክ ዋጋ መክፈል ይኖርብናል። እኛም ብንሆን እግዚአብሔርን ከወደድነው በዚህ በሰውነታችን ልናደርግ የምንችለው እርሱን በእውነት ማምለክ ብቻ ነው። የተፈጠርነው፣ የተዋጀነው፣ የተወደድነውም እግዚአብሔርን ለማምለክ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከእያንዳንዳችን ሕይወት የሚሻው ንጹሕና እውነተኛ አምልኮታችንን ነው። “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤” (ዮሐ. 4:23)

በአምልኮ ውስጥ የእግዚአብሔር ድምጽ፣ ምሪት፣ ፈውስ፣ መጽናናትና መፈታት አለ። አምልኮ ውስጣዊ መስዋዕት ነው። አገልግሎት ውጫዊ ነው፣ ነገር ግን መለኮታዊ፣ እውነተኛ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ አምልኮ ማንም የማይደርስበት ከውስጣችን ለጌታ የምናቀርበው መስዋዕት ነው። የነፍስ መስዋዕት ነው። አምልኮ እስትንፋስ ነው፤ ያለ እስትንፋስ ሰው ሕልውና አይኖረውም። አምልኮ ያን ያህል ውድ ነው።

አምልኮን መከራ ሐዘንና ጭንቀት አይበግረውም። በነዚህ ሁሉ የሕይወት ድቀቶች ውስጥ እግዚአብሔርን ከማምለክ የሚገታን ነገር አይኖርም፣ ግን የሰውን ልጅ ከአምልኮ የሚያርቀውና ሲያደናቅፈው የሚታየው፣ ቅጥ ያጣው ድሎቱ ነው። አለ ቅጥ የበዛ የቅንጦት ሕይወት እንኳን አምላክን፣ የራስንም ማንነት የሚያዘነጋ ነው። ስለዚህ በሚመችም ሆነ በማይመችም መንገድ ለእግዚአብሔር የሚገባውን የአምልኮን መስዋዕት ለማቅረብ የተጋን ልንሆን ይገባል።



## 5▸ የእግዚአብሔርን ታላቅነት መገንዘብ።

እግዚአብሔርን በመውደድ ራሳችንን መስዋዕት አድርገን በማቅረብ ስንመለከት የሚከተለው ክስተት የእርሱን ታላቅነት በሕይወታችን መገንዘብ ነው። በዚያን ጊዜ “እግዚአብሔር ሆይ! ታላቅ፣ ፃድቅና ኃያል ነህ፤” የሚለው ምስጢር ወደ ውስጣችን ዘልቆ ይገባል። ሁሉ የእርሱ ስለሆነ የእኛ ድርሻ ታላቅነቱን መረዳት ብቻ ነው።

## 6▸ የእግዚአብሔርን ውለታ ማስተዋል።

የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሁሉን ቻይነት የተገነዘበ ሰው ውለታውንም አብሮ የሚያስተውል ልብ አለው። ምክንያቱም የሆነው ነገር ሁሉ ከእርሱ እንደ ተገኘ አይዘነጋም።

ማስተዋል ምንኛ አስደናቂ ስጦታ ነው። እስራኤላውያን እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን አከናውኖላቸው እያለ በማስተዋል ጉድለት ምክንያት ከተደላደሉ በኋላ ክንዳችን አደረገልን በማለት መታበይና የጌታን ውለታ መርሳት ጀመሩ፤ የእግዚአብሔርን ውለታ ማስተዋል ተሳናቸው። ክንዳቸው አምላካቸው ሆኖ ጣዖት እስኪሆንባቸው ድረስ ያጕረሰ የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን እጅ ነከሱ። ምንኛ ልብ የሚሰብር ክዋኔ ነው?

እኛም ዛሬ የሆነውን ሁሉ በራሳችን ጥረትና ድካም እንዳደረግነው በማውራት የጌታን ውለታ በመርሳት አምላካችንን እንዳናሳዝን እንጠነቀቅ ዘንድ ይገባናል። ስለዚህ ይህን ውለታ ለዘላለም እንዳንረሳው በልባችን አትመን ማኖር ይገባናል።

## 7▸ በንጽሕናና በቅድስና ለእግዚአብሔር መኖር።

የእግዚአብሔርን ውለታ የሚያስተውል ሕይወትን ስናፈራ ውለታ የዋለልንን፣ ከትቢያ ያነሳንን፣ በስንት ሸለቆ ጠብቆ ያሳለፈንን አምላካችንን በአካሄዳችን እንዳንበድለው በመጠንቀቅ ራሳችንን በንጽሕናና በቅድስና ለእርሱ ክብር እናኖራለን። በታላቅነቱ ያየነው ልናመልከው የወሰንለት አምላክ ውለታውን የምናስበው ጌታ የማይሻውን ማንኛውንም የልባችንን ሸለፈት ማስወገድ ይገባናል። የውስጥ ቅድስናና ንጽሕና ያስፈልገናል። የአነጋገር፣ የአረማመድ የታይታ ቅድስና ሳይሆን የውስጥ የነፍስ ቅድስና ያሻናል። የኢሳይያስ ጩኸት ይህንኑ የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔርን አይቶ መልሶ ጉድለቱን የማያስተውል አይኖርም፤ ስለዚህ ጌታ ለኢሳይያስ የሰጠው ዕድል ለእኛም የሚያደርግልን አምላክ ስለሆነ መጠየቅ የእኛ ፈንታ ነው።

## 8▸ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት።

በንጽሕና የምንኖር ከሆነ የእግዚአብሔርን ድምጽ እንሰማለን። ለፈቃዱ እንድንኖር የሚያደርገን የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ዋናና አቢይ ጉዳይ ነው። አንገተ ደንዳና ያለመሆን፣ እልከኛ ያለመሆን የሚገኘው እግዚአብሔርን በመስማት ነው። በ1ሳሙ. 15:22 እንደ ተገለጸው መታዘዝ ከመስዋዕት ማዳመጥም ከአውራ ስብ ከማቅረብ ይልቅ እጅግ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ለመሆኑ በሚገባ እንመለከታለን። ቃሉን ሰምተን ስንታዘዘው በዮሐንስ ራእይ 1:10-12 እንደምንመለከተው ዮሐንስ የሚናገረውን ድምጽ ለመስማት ዘወር አለ። ይህም አንገተ ደንዳና ሳይሆን እግዚአብሔርን ለመስማትና ለመታዘዝ ያለውን ትህትና የሚያሳይ ነው። ያኔ ዮሐንስ ጌታን በክብሩና በሞገሱ በታላቅነቱና በኃይሉ ተመለከተው። ሰገደለትም። አንገተ ደንዳኖች እግዚአብሔርን መስማት



ስለማይሹ፣ የእግዚአብሔርን ውበት አያዩም። የጌታን መንገድ አይረዱም። የእርሱን ፈቃድ አይለዩም።

## 9▸ በእግዚአብሔር ርኅራኄ መመላለስ።

የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ ሰው በርኅራኄ የተሞላ ነው። ለሌላው የማሰብ፣ የሌላውን ሸክም የመሸከም ሕይወት የሚገኘው በርኅራኄ ከተሞላን በኋላ ነው። ለድሆች ማዘንና ለሚጨነቁት መልካም መሆን የርኅራኄ ሕይወት ውጤት ነው። የርኅራኄ ሕይወት ከግድየለሽነት ሕይወት የነፃ ነው። ለሚጠፉት መራራትና መፈለግ የእግዚአብሔር ታላቅ ፈቃድ ነው። የማይራራ ሰው ለታላቁ ተልዕኮ ኃላፊነት ግድ የለውም። የማይራራ ሰው፣ ለነፍሳት ደኅንነት ግድ የለውም። እንግዶችን የሚቀበል ሰው የርኅራኄ ሰው ነው። ርኅራኄን የተሞላ ሰው ሌላውን ያከብራል።

## 10▸ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መጽናት።

የሚራራ ሰው፣ በአምላኩ ኪዳን መግባት አይጠራጠርም አያፍርምም፤ የመሐላን ሕይወት እንድንለማመድ የሚያደፋፍረን ሳይሆን በአምላካችን ተማምነን ቃል ኪዳን እንድንገባ የሚያነቃቃን ነው። እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ስለሆነ፣ በእርሱ ስም የምንገባውን ኪዳን እንድንጠብቅ ሲያሳስበን ነው። ስሙ ይረከስ ዘንድ እግዚአብሔር አይፈልግም። ለሌሎች የገባነውን ቃል፣ እንዴ በጌታ ስም ገብተናልና ባንፈጽመው የእርሱን ስም ስላረከስን እንጠየቅበታለን። በአዲስ ኪዳን ሁለት ኪዳናት ይገኛሉ።

1ኛው ከእግዚአብሔር ጋር የምንገባውን ኪዳን የሚመለከት ሲሆን፣

2ኛው ደግሞ ከሰዎች ጋር የምንገባውን ኪዳን የሚጠቁም ነው። በአደባባይ ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታን ስንቀበል ኢየሱስ ከዛሬ ጀምሮ ጌታዬና አምላኬ ይሆናል ብለን ቃል ኪዳን እንገባለን። ያ ኪዳን ለዘላለም

መጠበቅ አለበት።

በተጨማሪም ጋብቻን በምንፈጽምበት ወቅት በእግዚአብሔርና፣ በእግዚአብሔር ጉባኤ ፊት ቃል ኪዳን እንገባለን፣ ይህም ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ስም የፈጸምነው ስለሆነ፣ መጠበቅ የግዳችን ነው። ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ጋር ሊያለያየን ሲሻ እንደምንም ብሎ የሚወስደው እርምጃና ውጊያ በገባነው ጥብቅ ቃል ኪዳን ላይ ነውና መጠንቀቅ ይኖርብናል።

### 11▸ ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ።

ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር የመጣበቅን፣ የሙጥኝ ማለትን የሚያሳይ ምልክት ነው። በዚህ ዘመን የክርስቶስ መገለጥ በቀረበበት በዚህ በመጨረሻው ጊዜ እኛ ማድረግ የሚኖርብን ዋናና ትልቁ ነገር እግዚአብሔርን አጥብቀን መያዝ ነው። ሁሉም ነገር ቢቀርም እንኳ እግዚአብሔርን ለመልቀቅ የሚያስብ ልብ እንዳይኖረን መጠንቀቅ አለብን። የሚያዛልቀው እርሱ ብቻ ነው። ምንም ነገር ከእርሱ እንዳይለየን ያስፈልጋል። (ሮሜ. 8:35)

### 12▸ እግዚአብሔርን ማክበር።

ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣበቅን እግዚአብሔርን እናከብረዋለን። በፊታችን ያደረገውን ትልቅ ነገር ተመልክተን እግዚአብሔር ክብራችን ይሆን ዘንድ የጌታ ቃል ያሳስበናል። ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣበቅን በሕይወታችን ገብቶ የሚሸነግለን ክብርና ሞገስ አይኖርም። ክብራችን እግዚአብሔር ይሆናል። ሞገሳችን፣ መከታና እረኛችን ይሆናል። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው እርሱን እንፈራ ዘንድ ነው። እርሱ ክብራችን ነው።



# ክፍል- ሦስት

# በራእይ ማደግ



# ም ዕ ራ ፍ   ስ ም ን ት

## ራ እ ይ   ም ን ድ ነ ው ?

“ንጉሥ አግሪጳ ሆይ:- ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልሁም።” (ሐዋ. 26:19)

ራእይ በመንፈሳዊው ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ ከመንፈሳዊ አሠራር ውጭ የሚገኙ ሰዎች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። የራእይን ምንነት ለመገንዘብና ብያኔም ለመስጠት፣ የአተረጓጎማችን ይዘትና አስተያየት ወሳኝ ይሆናል። ክርስቲያኖች ራእይን፣ ሌሎች የማያምኑ ወይም ዓለማውያን እንደሚያዩት፣ እንደሚተረጉሙትና እንደሚበይኑት ዝም ብለን የጅምላ ትርጉም ከሰጠነው፤ ከቶም የራእይን ምንነት ተረድተናል ብለን በሙሉ አፋችን ለመናገር አያስደፍረንም። በተለይ ሰማያዊው ራእይ ለክርስቲያኖች ልዩ ትርጉም እንዳለው ማወቅ ይገባናል። ይኸንንም እውነት የምንገነዘበው በእርግጥም የራእይን ምንነት ስንረዳ ብቻ ነው።

በዚህ መጽሐፍ የራእይን ምንነት በጉልህ ሊያስረዱን የሚችሉትን ዝርዝር ነጥቦችን በስድስት ከፍለን ለማየት እንሞክራለን። እግረ መንገዳችንንም እንደ እግዚአብሔር ቃል “ራእይ ማለት ምን ማለት ነው?” የሚለውን ጥያቄ መልስ በመስጠት የራእይን፣ በተለይም የሰማያዊ ራእይን ወሰነ ትርጉም በአጠቃላይ መልኩ ለመስጠት እንሞክራለን። በዚህ መሠረት እንግዲህ:-

አንደኛ ራእይ ማለት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መለኮታዊ መገለጥ ነው። ራእይ ከዕለት ተዕለት ልምምድና ከተፈጥሮአዊ አሠራር ውጭ እግዚአብሔር ለልጆቹ መሠረታዊ ነገሮችን የሚገልጥበት መለኮታዊ አደራረግ ነው። ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:-



1. እግዚአብሔር ከሰው ግምት ልምምድ ውጭ ራሱን /ክብሩን/ የሚገልጽበት፤

2. እግዚአብሔር በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ሊፈጽም ያለውን እቅዱንና ዓላማውን የሚገልጽበት፤

3. የገለጠውን ዓላማና እቅድ በተግባር የመተርጎሚያ ስልቱንና ዘዴውን የሚያሳውቅበት ነው። (የእርሱን ሥራ በእርሱ መንገድና ኃይል የሚያከናውንበትን የሚያሳይበት አሠራር ነው)

በሁለተኛ ደረጃ የራእይን ወሰነ ትርጉም ሠፋ አድርገን ስንመለከተው:- ራእይ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሆን መለኮታዊ ምሪትን የሚሰጥበት ዓይነተኛው የመገናኛ ዘዴ ነው። በዚህም ምሪት ውስጥ እግዚአብሔር ሥርዓትን ይደነግጋል፤ ምክንያቱም ያለ መለኮታዊ ምሪት፣ ራእይ ከቅዠት አይለይም፤ ያለ መለኮታዊ ምሪት ሥርዓትንም መደንገግ አይሞከርም። እግዚአብሔር ሕዝብን ሥርዓት ለማስያዝ ድንጋጌን ይሰጣል፤ ድንጋጌን ለመስጠት መለኮታዊ የሆነውን አመራሩን በራእይ ይገልጻል፤ አለበለዚያ “ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን በሆነ ነበር” የሚለው ቅዱስ ቃል ባላስፈለገም ነበር።

መረን ማለት በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥርዓት የለሽ፣ ስድ የተለቀቀ፤ ማለት ነው። ታዲያ በሥርዓተ አልበኝነትና በስድነት ውስጥ የሚገኘውን ሕብረተሰብ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድና ሐሳብ ቢገለጽለት ውኃ በድንጋይ ላይ እንደማፍሰስ ያህል እንጂ፣ ፍሬያማ ይሆናል ብሎ ለመገመት አያስደፍርም። ከዚያ ይልቅ አስቀድሞ፣ ሕዝቡ ስድነቱን፣ መረንነቱንና ሥርዓት የለሽነቱን፤ የሚያርቅበት፣ የሚያስተካክልበትና ለመለኮታዊ ሥርዓት የሚገዛበትን፤ መለኮታዊ ምሪት ከእግዚአብሔር ያገኝ ዘንድ ያስፈልጋል። ሥርዓትና ድንጋጌ በራእይ በኩል ከአምላኩ ማግኘት ይገባዋል። አለበለዚያ ግን በመረንነቱ ይጠፋል።

በሦስተኛ ደረጃ ራእይን ስንበይነው:- ራእይ ከመንፈሳዊ አሠራር አንጻር፣ በሰማይ የሚከናወነውን መለኮታዊ እቅድና ተግባር በምድር ላይ

እንዴት እንደሚፈጸምና እንደሚደረግ የሚገለጽበትና የሚተረጎምበት አምላካዊ መመሪያ ነው። እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጥ እንዲያው በቁሙ፣ እንደ ተውኔት የሚታይ፣ ትርኢት አድርጎ ሳይሆን በውስጡ እጅግ ታላቅ መንፈሳዊ ረብ ወይም ቁምነገሮች ያላቸውን መገለጦች፣ ማስተዋሎችና ጥበቦችንም ጭምር አያይዞ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በሰማያዊው ሥፍራ የሚያሳየውንና የሚገልጠውን ራእይ፣ በዚህ በምንኖርበት ዓለም ውስጥ፣ ተጨባጭና ተግባራዊ ለማድረግ፣ እነዚህ መገለጥ፣ ጥበብና ማስተዋል የተሰኙት ዋና ዋና መገልገያዎች ወሳኞች ናቸው። በማቴዎስ ወንጌል 16:17 ላይ እንደ ተገለጸው ጴጥሮስ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ከሌሎች ሐዋሪያት ቀደም ብሎ "አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነህ" በማለት ሲገልጽ፣ ጌታ በጊዜው የሰጠው ምላሽ እጅግ መሠረታዊ ቁም ነገር ነበር። ይኸውም "በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።" ብሎ ነበር የመለሰለት። መንፈሳዊ እውነታዎች ምንጫቸው ሰማያዊ ነው። ለማንኛችንም የተገለጠልን እውነት ምንጩ ከላይ ከሰማይ ከአርያም ካልሆነ በቀር ከቶም ሌላ መገኛ ይኖረዋል ተብሎ ማሰብ አላዋቂነት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ስለ ተገነዘበ ነበር "ከሰማይ ለታየኝ ራእይ" ያለው። በተጨማሪም ነቢዩ ዳንኤል መልአኩ ይዞ ያመጣለትን ራእይ፣ "ከሰማይ የተገለጠልህን" በማለት ነው ያሳወቀው፤ ዮሐንስም ያንን ሰፊና አስገራሚ ራእይ የተመለከተው፣ ከሰማይ በተገለጠለት መሠረት ነው። እነዚያንም ራእዮች መረዳት የቻለው ሰማያዊ ጥበብና ማስተዋልን፣ ከመገለጡ ጋር ስለ ተሰጠው ነበር። ለዳንኤልም ከራእዩ ጋር ሰማያዊ መገለጥ እንደ ተሰጠው ሲያረጋግጥለት ቃሉ "...ዳንኤል ሆይ:- ጥበብና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።" ይለዋል። (ዳን. 9:22)

በአራተኛ ደረጃ ራእይን ስንበይነው ሰማያዊ ራእይ ማለት እግዚአብሔር ብቻ የሚያየውን፣ ማየት መቻል ማለት ነው። ይህ ሲባል ሰው በሰብእናው፣ በሥጋ ለባሽነቱ ብቻ፣ ማየት የማይችለውን ማየት መቻል



ማለት ነው። ለዚህ ነው ራእይ ወይም መገለጥ የሚለውን ስያሜ ያገኘው። ሰው በሥጋ ዓይኑ የሚያየውና የሚገነዘበውን ሁሉ ራእይ ወይም መገለጥ ብለን አንጠራውም። ራእይ በመንፈስ ዓይን ማየት ወይም የመንፈስ ዓይን ተገልጦ መመልከትና ማስተዋል ነው። ማንኛችንም ብንሆን ራእይ አይተናል ብለን መናገር የምንችለው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ በመንፈስ ሆኖ የሚያየውን እኛም መንፈሳዊ ዓይናችን ተከፍቶ የማየቱ ዕድል የገጠመን ጊዜ ብቻ ነው። አለበለዚያ ግን፣ እውነተኛ፣ መለኰታዊና መንፈሳዊ ራእይ አየን ብለን መናገራችን ስህተት ይሆንብናል። ራእይ ከሰብዓዊነትና ከሥጋዊ ልምምድ አልፎ የሚገኝ ጥልቅ ምስጢር ያለው ነውና።

በአምስተኛ ደረጃ ራእይ፣ ከአገልግሎት ጥሪ ጋር፣ ለመለኰታዊ አሠራር ያግዝ ዘንድ የሚሰጥ መለኰታዊ ምሪት ነው። እግዚአብሔር ለጥሪው ማከናወኛ፣ የአገልግሎትን እቅድና አፈጻጸምን የሚያስገነዝብና የሚመራው በመለኰታዊ መገለጥ ስለሆነ፣ ራእይ የሚባለውም ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ከጥሪአችን ጋር የሚሰጠን መመሪያና፣ በተግባርም ልንተረጉመው የሚገባን እቅድ ይኖረዋል፤ ሲጠራን በዓላማ ነውና። ይህም ቢሆን የተሰጠን ራእይ በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱሳን ተመዝኖ የሚጸና መሆን አለበት። ራእይ በቃሉ ውስጥ የተሰጠውን ተስፋ ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆንልን ጌታ የሚሰጠን መመሪያ እንጂ ከቃሉ ውጭ የሚወጣ አይደለም። ስለዚህ ነው ቃሉ የሁሉም ነገር መሠረትና መለኪያ የሆነው። በቃሉ ተፈትኖ የማያልፍ ነገር ምንጩ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

ስድስተኛው የራእይ ወሰነ ትርጉም፣ አጠቃላይ የሆነውን የራእይን ብያኔ ይመለከታል። ይኸውም ራእይ የማያምኑትም ቢሆኑ እንደሚተረጉሙት፣ በሥጋዊ ዓይን ሊታይ የማይችለውን፣ ማለትም የማይጨበጥ የማይዳሰስና፣ ገሃድ ያልወጣውን ነገር፣ በዓይነ ሕሊና በመቃኘት፣ ነገሩ የሌለ እንኳ ቢሆንም፣ አእምሮን አንቅቶ በመንፈሳዊ ርዕዮት መመልከትና ያንንም በአካልና በሥጋ በተግባር ተገልጦ እንዲተረጎም የማድረጊያው ሂደት ነው። ይህ ዓይነቱ የራእይ ትርጉም እንግዲህ፣ ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች

የአገልግሎት እቅድና አሠራር ጋር እምብዛም የማይጋጭ ቢሆንም፣ በአብዛኛው በዚህ ትርጉም መሠረት ሲጠቀሙበት የሚገኙት በማሕበራዊ አገልግሎት (በሥራ ላይ) የሚገኙ ሰዎች ናቸው።



# ምዕራፍ ዘጠኝ
# በራእይ መኅልመስ



# ም ዕ ራ ፍ   ዘ ጠ ኝ

## በ ራ እ ይ   መ ሳ ል መ ስ

ራእይ በምዕራፍ ስምንት እንደ ተመለከትነው ከሆነ፣ ሰው በራእይ እንዴት ነው ማደግ የሚችለው? ምስጢሩስ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ልንጠይቀው የሚገባን ጉዳይ ነው። ይህንንም ምስጢር ለመረዳት ስድስት መሠረታዊ ሂደቶችን እንድናጤን ያስፈልጋል። በእርግጥ በራእይ የመብሰልና የማደግን ምስጢር ለመረዳት የሚያግዙን ሂደቶች በርከት ያሉ ቢሆኑም፣ ለጊዜው ከዚህ በታች ዘርዘር አድርገን በምንመለከታቸው ስድስት ነጥቦች ላይ ብናተኩር መሠረታዊ ነገሮችን ለመቅሰም በቂ ይሆኑናል።

### 1▸ የራእይን ዓላማ መረዳት

በራእይ የማደግ ምስጢር የመጀመሪያው ደረጃ፣ የራእይን ዓላማ መረዳት ነው። ይህም ማለት ከላይ እንደገለጽነው፣ ራእይን እግዚአብሔር ሲሰጠን ወይም ሲያሳየን፣ በፊት ለፊታችን እንደሚገኘው እንደ ሲኒማ በአቡጀዲ ላይ እንደምናየው የምስል ተውኔት፣ በሕልም ዓለም ውስጥ ገብተን ተመልክተን፣ ከዚያ በኋላ አድንቀን፣ በዚያ ላይ እንድናቆም አይደለም፤ ራእይ ሲሰጠን ከዚያ ባሻገር ላለ ዓላማ ነው። ይኸውም ለአገልግሎትና ለሕይወት እጅግ የሚጠቅም መለኮታዊ ምሪት እናገኝ ዘንድ ነው። ራእይ የእግዚአብሔርን እቅድና መመሪያ የምናይበትና የምንሰማበት ዓይነተኛ መለኮታዊ የመገናኛ መንገድ ስለሆነ፤ ከእግዚአብሔር በምንሰማበት ወቅት በጥንቃቄና በማስተዋል ማዳመጥ ይገባናል። አንዳንድ



ጊዜ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የነቢያትን ንግግር ግምት ባለመስጠት፣ ንቀን በቸልታ ስናልፍ እንገኛለን። በመሠረቱ የነቢያትን ንግግር ቸል ማለት የሚጎዳውና የሚያሳዝነው፣ የሚናገሩትን የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ብቻ ሳይሆን፣ መልእክቱን የላከውን እግዚአብሔርን እንደ ሆነ ልናውቅ ይገባናል። ይህን ነጥብ ግልጽ የሚያደርግልን እግዚአብሔር ለሳሙኤል የመለሰለት መልስ ነው። "የሚፈርድልንም ንጉሥ ስጠን ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው፤ ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው:- በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ።" (1ሳሙ. 8:6-7) የአገልጋዮችን መልእክት መናቅ ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኃያልና የሁሉም ገዥ የሆነውን እግዚአብሔርን መናቅ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናገኘው ብዙውን ጊዜ የእስራኤላውያን ውድቀት የመጣው ከዚህ ዓይነቱ ተደጋጋሚ ድካማቸው በኋላ ነበር። አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል የገለጠላቸውን ራእይ ለመስማት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀሩ፤ ከዚያም፣ ከብዙ ቅጣትና ውድቀት በኋላ የተቀበሉትን ራእይ፤ ምግባራዊ ያደርጉ ዘንድ ሲታዘዙ፤ ጭራሽ ለራሳቸው መመኪያና መታበያ እንዲሆን ሥርዓትና ወግ በማድረግ ተጠቀሙበት። እግዚአብሔር በሁለቱም አሠራራቸው አልተደሰተም፤ የልቡ አልሆነለትም፤ እንደ ፈቃዱ አልተከናወነለትም፤ እንደሚያሻው አልተፈጸመለትም።

እኛም የምንቀበለውን ራእይ እስራኤላውያን እንዳደረጉት ከእግዚአብሔር ፈቃድና መሻት ውጭ በማልከስከስ ወግና ልማድ አድርገን የራሳችን ክብር ከፍ እንዲል የምንጠቀምበት ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ባለው ዘላለማዊ እቅድ መሠረት አገልግሎታችንን በፈቃዱ መሠረት የምንፈጽምበት መመሪያ መሆኑን ደጋግመን ማስታወስ ይገባናል። እንግዲህ የራእይ ዋንኛው ዓላማ የሚባለው ይኸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም "...ከሰማይ ለታየኝ ራእይ እንቢ አላልኩም" ያለው ይህንን ምስጢር ስለ ተገነዘበ ነበር።

እግዚአብሔር ሰፊና ዘላለማዊ እቅድ ስላለው፣ ራእይን ሲሰጥም ለአንድ ግለሰብ ብቻ ጠቀሜታ፣ ክብርና፣ ትምክህት ብሎ አይደለም። በእርግጥ ራእይን በአንድ ግለሰብ በኩል ቢያስተላልፍም፤ የራእዩ ዓላማና ውጤት ባንድ ግለሰብ ላይ ብቻ በማተኮር በዚያው ተወስኖና ተመጥኖ እንዲፈጸም አይደለም። ያንን ግለሰብ የተጠቀመው ራእዩን ለሕዝቡ ያስተላልፍ ዘንድ፣ እንደ መልእክተኛ አድርጎት ነው እንጂ ራእዩ በግለሰቡ በኩል ሲተላለፍ ግለሰቡን ልዩ ሰው አድርጎ፣ ለማሳየትና የመለኮታዊ ዘላለማዊ እቅዱም በእርሱ ላይ ብቻ እንዲያተኩር አይደለም። በግለሰቡ በኩል የሚተላለፈው ራእይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንድያንጽና መንግሥቱንም የማስፋፋት ዓላማ ለማከናወን መሆኑን አጥብቆ መረዳት ከብዙ ስህተት ይጠብቀናልና ቸል አንበል።

ማንም ባለ ራእይ እግዚአብሔር በሰጠው መልእክት ላይ የይገባኛልና የባለቤትነት መብት የለውም። ራእዮችን በሙሉ ሰብስቦ፣ ለራሱ ብቻ እንደ ተሰጠው በማድረግ እንደ ግል ንብረቱ አድርጎ ማየት አይችልም። ራእይን የመስጠት፣ የመቆጣጠርና፣ የመፈጸም መብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር በልጆቹ በኩል ራእይን ያስተላልፋል፤ እግዚአብሔር በመረጣቸው ሰዎች በኩል የራእዩን አደራረግ ይቆጣጠራል፤ እግዚአብሔር በለያቸው ሰዎች በኩል ራእዩን በተግባራዊነት ይፈጽማል። ነገር ግን የራእይ ዋነኛው ዓላማ ከዚህ ውጭ ከሆነ፤ ጥያቄ አለበት ማለት ነው። የጎደለው ነገር አያጣምና በመንፈስ ሆኖ መፈተኑ ለእግዚአብሔር ልጆች የተሰጠ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው።

ዘመናችን የዓለምን ሕብረተሰብ በእኔነት፣ በግለኝነትና በራሴነት የዋጠበት ዘመን ስለሆነ፣ በዚያው ልክ በአቢያተ ክርስቲያናትም ውስጥ ይኸው መንፈስ ሠርጾ ገብቶ፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይተላለፍና፣ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የሚሰጠውን ራእይ ሳይቀር የኔ ነው ወደ ማለቱ ደረጃ እየገፋ መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብና ግምት፣ ከራእይ ትርጉምና ዓላማ ፈጽሞ የራቀና ብልሹ ዝንባሌ ነው።



ራእይ የአንድ ግለሰብ አይደለም። ራእይ ሲሰጥ እግዚአብሔርም ዓላማዬ ብሎ የሚያነጣጥረው በግለሰብ ላይ ሳይሆን፤ በእግዚአብሔር መንግሥትና፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ነው። ስለዚህ ከዚህ ዓላማ ውጭ እንዲሆን እግዚአብሔርን አፈናቅለን በግለሰብ ላይ ያተኩር ዘንድ ለማስገደድ እኛ ማን ነን? የሚገርመው ነገር ሳናውቅም ሆነ በድፍረት በአሁኑ ወቅት ልማድ አድርገን የምንጠቀምበት የራሳችንን ቋንቋ አጐልምሰናል (አሳድገናል)። ይኸውም በተለያየ ሥፍራ ማንነታችንን ለማስተዋወቅ በምንሻበት ጊዜ ሁሉ "የኔ ራእይ፣ የኔ አገልግሎት፣ የኔ... የኔ... የኔ..." ማለት ይቀናናል። ይህን በማድረጋችን በስህተት ዓለም ውስጥ ልብ ሳንለው ሽርተት ብለን መውረዳችንን ግን አልተገነዘብነውም። ይህን የእኔነትን በሽታ በማስመልከት፣ መጨረሻውንም በማሳየት ሐዋርያው ጳውሎስ በሚገባ በሮሜ ምዕራፍ 7 ላይ ገልጾታል።

ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚሁ ምዕራፍ የሮማውያንን የነፍሰ ገዳይ ቅጣትን እንደ ዘይቤ በመጠቀም ምርር ብሎ የተናገረው ንግግር እጅግ ውስጣችንን ሰርስሮ የሚሰማን አገላለጽ ነው። በሮማውያን ዘመን አንድ ነፍሰ ገዳይ፣ መግደሉ ከታወቀና ከተረጋገጠ በኋላ፣ የወቅቱ ሕግ የሚፈርድበት በዚህ መንገድ ነበር ይባላል። ይኸውም ነፍሰ ገዳዩ የገደለውን ሰው ሬሳ፣ ከራሱ እስከ እግሩ ድረስ በጀርባው እንዲሸከምና፣ በየከተማው እንዲዞር ይደረጋል። ይህም ቅጣት የሚፈጸመው፣ ለደቂቃዎች ወይም ለሰዓታት ወይም ለቀናት ብቻ አልነበረም። ነፍሰ ገዳዩ ከዚያ ከተሸከመው አስከሬን ጋር ተንገላትቶ፣ በሸክሙ ክብደት ተጐድቶ፣ ከሬሳው በሚወጣው መጥፎ ጠረን ገምቶ እሱም በተራው ሕይወቱ እስከታልፍ ድረስ ነበር። ምንኛ አሰቃቂ ቅጣት ነው! ሐዋሪያው ጳውሎስም፣ እኔነቱን የተመለከተው ልክ እንደ ሬሳው ነው። ለዚህም ነበር ምርር ባለ አገላለጽ "ከዚህ ሟች ከሆነው ሥጋ ማን ይለየኛል" በማለት እሪታ ያሰማው። እኔነት ሞቶ እንደ ከረመ በድን በላያችን ላይ ተጭኖ ራሳችንን ለማጥፋት የማይመለስ በሽታ ነው። እኔነታችን ጤናማና ግዙፍ የሆነውን መንፈሳዊ

ሕይወታችንን አበስብሶ ለበሽታና ለድካም የሚሰጥ ነገር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጥ ለራሱ ክብርና ለመንግሥቱ ማስፋፊያ እንጂ፣ የግል ራእይ የሚባል ነገር ስላለ አይደለም። ከዚህ ውጭ ራእይን መገንዘብ፣ የራእይን ዓላማ መረዳት አይሆንም። እንግዲህ በራእይ ለማደግ ይህ የማይገሰሰውን የእግዚአብሔርን ዓላማ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

### 2▸ ለተገለጠው ራእይ ታማኝ መሆን።

በራእይ የማደግ ምስጢር፣ ለተገለጠው ነገር ታማኝ መሆን ነው። በራእይ ለማደግ ከፈለግን፣ እግዚአብሔር ለገለጠልን ነገር ታማኝ እንድንሆን የተገባ ነው። ምንም ጊዜ ቢሆን የእግዚአብሔር ጉዳይና ታማኝነት ተነጣጥለው የሚታዩ ነገሮች አይደሉም። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚያሳየን ለሚሰጠን ምሪትና ለሚገልጥልን ራእይ ታማኝነት ካልተገኘብን በራእይ ማደግ አንችልም። በራእይ አድገን ፍሬን ማፍራት የምንችለው እንዲሁም ከጅማሬ ራእይ ወደ ታላቅ ራእይ መራመድ የምንችለው፣ በቅድሚያ ከእኛ የሚፈለገውን ታማኝነት አሟልተን ስንገኝ ነው፤ እንግዲህ ይህ ሌላው በራእይ የማደግ ምስጢር ነው።

### 3▸ ራእዩን በሥራ ላይ ማዋል።

በራእይ የማደግ ምስጢር ለማወቅ እግዚአብሔር ያሳየንን የተከበረ ነገር በሥራ ላይ ለማዋል ሙሉ ፈቃደኝነት ይኖረን ዘንድ ያስፈልጋል። ይህም ማለት ራእይን፣ በንድፍና፣ በሃሳብ ደረጃ እንዳለ እንዲቀር ሳይሆን፣ ያንን ሃሳብ እግዚአብሔር በሚሰጠው ምሪት መሠረት ተጨባጭና ገሃድ ለማድረግ፣ የሚጠይቀውን የኃላፊነት ግዴታ በፈቃደኝነት መቀበል መቻል አለብን። እጅግ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ዛሬ አያሌ አገልጋዮች እግዚአብሔር ራእይን እንደገለጠላቸው ቢናገሩም፣ ለተጨባጭነቱ



አንዳችም የፈቃደኝነት ዝንባሌ አለማሳየታቸው ነው። እግዚአብሔር ራእይን በሰማይ በንድፍና በሃሳብ ደረጃ ሲከወን የሚያሳየው፣ በምድር ላይ ያ ሃሳብና ንድፍ ግዙፍ ሆኖ ታይቶ፣ ተጨባጭ ይሆን ዘንድ ዋነኛ ፈቃዱ ሆኖ ነው። ታዲያ አገልጋዮች ራእይ እንደ ተገለጠላቸው ብቻ አውርተው፣ ያዩትን ራእይ በምድር ላይ ገሃድ ለማውጣትም አንዳችም ጥረት ባያሳዩ ግን ምንኛ የሚያሳዝን ጉዳይ ነው? ራእይ ተጨባጭ ካልሆነ ካልታየና ካልተዳሰሰ፣ ዋጋ አይኖረውም። ለእግዚአብሔር መንግሥትም የሚሰጠው ጥቅም የለም።

በመሠረቱ በራእይ አተረጓጎም ሂደት ላይ፣ ሌላም አማራጭ አለ። ይኸውም ራእይን ከእግዚአብሔር ለመቀበል እድልን ያገኙ ወገኖች፣ ለተግባራዊነቱ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው ድረስ እነርሱ የመሯሯጡና የመተርጎሙ አቅሙና ጸጋው ከሌላቸው፣ ራእዩ ያሳደረባቸው የአገልግሎት ሸክም ሳይቀንስ፤ ጸጋ ያላቸውን ሰዎች እግዚአብሔር አገናኝቶአቸው፣ ራእዩ ገሃድ በመውጣት ተጨባጭነትን ያገኝ ዘንድ በጸሎት የመማጸንም የአማራጭ እድል አላቸው። ምክንያቱም ራእይን ያየ ሁሉ፣ ተጨባጭ የማድረግም ችሎታ አለው የሚል አመለካከት ሊኖረን አይገባምና። ለዚህም ነው እግዚአብሔር በእርሱ መንግሥት ግንባታ ውስጥ፣ ለአገልግሎት ቀናነት፣ የተለያየ የሥራ ድርሻ በማደላደል ያስቀመጠው። ይኸውም እግዚአብሔር ነቢያት፣ ሐዋሪያት፣ አስተማሪዎችና የመሳሰሉትን ከፍተኛ የአገልግሎት ዘርፍ ምድቦች አስቀድሞ በማደላደል አስቀምጧል።

በራእይ አፈጻጸም ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናገኛቸው ከፍተኛዎቹ የአገልግሎት ዘርፎች ታላቅ ጠቀሜታ አላቸው። ለምሳሌ ነቢያት ያያሉ፣ ሐዋሪያት ይተረጉማሉ (መሠረት ይጥላሉ)፤ ወንጌላውያን የምስራቹን ቃል ይናገራሉ፤ እረኞች የመጡትን ይመግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ያሰማራሉ፤ አስተማሪዎች ምስጢርን በመግለጥ ሕዝቡን ወደ ብስለት ይመራሉ። በዚህ ዓይነት መልክ ነው፣ የእግዚአብሔርን አገልግሎት እንደ መረብ ተጣምረው በመፈጸም መንግሥቱን የሚያስፋፉት።

### 4▸ በራእይ ለማደግ ፈቃደኛ መሆን።

በራእይ የማደጉ ምስጢር ለመረዳት ደግሞ፣ በአስተሳሰባችን በአመለካከታችን በብስለታችን ዕድገትን ለማሳየት መሻትና ፈቃደኝነቱም እንዲኖረን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሰማያዊ ራእይ ባለንበት ወይም ከዚህ በፊት በነበርንበት የእድገትና የብስለት ደረጃ ብቻ ተወስነን እንድንቀር ሳይሆን ከእድገት ወደ እድገት፣ ከብስለት ወደ ብስለት እየተረማመድን ደረጃችንን እንድንጨምር ለማድረግ የሚሰጠን ነገር ነው። ስለዚህ ነው ራእይ በባሕርዩ መለኮታዊና ሰማያዊ ሊሆን የቻለው። በእርግጥ ራእይ ለጀማሪ ተቀባዮቹም ሆነ እድገታቸው ለራሳቸው ላላስተማመናቸው ሰዎች አስፈሪ ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ሰማያዊ ራእይ፣ መለኮታዊ ስለሆነ ወደ ታላቅ ልምምድ የማደግና የመዘርጋትን መንፈሳዊ ኃይል በማሳወቅ ሂደት ላይ ተቀባዩን፣ ከአድናቆትና ከግርታ ጋር ፍርሃት ውስጥ ስለሚከት ነው። ለምሳሌ ሙሴ ቁጥቋጦው ሲቃጠል አይቶ የእግዚአብሔርን ድምጽና ጥሪ በሰማ ጊዜ በፍርሃት ተዋጠ። “ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።” (ዘጸ. 3:6) የእግዚአብሔር ፈቃድም በራእያችንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግና እንድንበስል ነው። ወደድንም ጠላንም ሰማያዊውን ራእይ ስንቀበል አስቀድሞ የሚታወሰንና የሚታየን ታናሽነታችን ስለሆነ፣ ቶሎ ብለን ወደ ጌታ፤ “ኧረ እኔ አልችልም” የሚለው ጩኸታችን ማሰማት ይቀድመናል። እግዚአብሔር ግን ማንነታችንን ሳያውቅ ራእይን አይሰጠንም። ከቶም እርሱ የማያውቀው ነገር የለም። ቢሆንም እርሱ ምንም እንኳ ታናሽ መሆናችንን እያወቀ ያንን መለኮታዊ ትዕይንት የሆነውን ራእይ ሲያሳየን ከጎኑ “አዎ እኔ ደካማነትህንና ታናሽነትህን አውቃለሁ። ቢሆንም ኃይሌ በድካምህ ይፈጸም ዘንድ ፈቃዴ ነውና አይዞህ” ማለቱ የማይቀር ነው። ከዚህ በኋላ ደግሞ የኛ ድርሻ ከራእይ ወደ ራእይ የማደግ ፈቃደኝነታችን መጨመር ይሆናል። ይኼ ነው በራእይ የማደጉ ምስጢር። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ



“የኋላዬን ትቼ ወደፊት እዘረጋለሁ” በማለት በራእይ የማደጉ ምስጢር ምን እንደሆነ የገለጸው።

### 5▸ ራእይን ተጨባጭ ማድረግ።

በራእይ የማደጉ ምስጢር እግዚአብሔር ያሳየንንና የገለጸልንን ራእይ፣ ከሰው ባሕል፣ ልማድና ወግ አውደ መሠረት ተግባራዊና ተጨባጭ ለማድረግ መቻል አለብን። በመሠረቱ የዓለም ሕብረተሰቦች፣ እንደ አካባቢያቸው ልዩነት የተለያዩ ባሕል፣ ልማድና ወጎች አሏቸው። ሁሉም እንደራሱ ባሕል፣ ልማድና ወግ ይኖራል። አሜሪካዊው እንደ ተወለደበትና እንዳደገበት ባሕል ይኖራል፤ ነገራትንም በዚያው መንገድ ይገነዘባል። ኢትዮጵያዊውም እንደዚሁ፤ ያሳደገውና ያጎለመሰው ጠብቆ ለወግ ለማዕረግ ያበቃው ባሕልና ልማድ አለው፣ ከዚህ በፊትም ሆነ፣ ከአሁን በኋላ ነገራትን መገንዘብ የሚችለው በበቀለበት ባሕልና ልማድ መሠረት ነው። ከዚያ ግንዛቤ ውጭ ለሚመጡ መልእክቶች እምብዛም ከራሱ ጋር ለማዋሃድ ስለሚከብደው በአብዛኛው ባዕድነት እንዲሰማው ያደርገዋል። ስለዚህ ይህንን ችግር ቀላል ለማድረግ፣ አንድ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራእይ በተቀባዩ ሕብረተሰብ ባሕልና ልማድ አውደ መሠረት ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ እንዲኖረው ይገባል። ለምሳሌ አንድ አገልጋይ ለኢትዮጵያውያን የሚሆን ራእይና መልእክት ካለው አስቀድሞ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ባሕልና ልማድ ማወቅ ይኖርበታል። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የከበረውን መልእክቱን ይዘቱንም ሳይቀንስ በኢትዮጵያውያን አቀራረብና አተረጓጎም፣ ተጨባጭ ማድረግ ለጥሩ ውጤታማነት አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ይህም ራእይን ለተቀበለው ሰው፣ አማራጭ ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትም እንደ ሆነ አስቀድሞ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 6▸ ራእይን መፈተን።

በራእይ የማደጉን ምስጢር ለመገንዘብ ደግሞ:- እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ መፈተንና መመርመር ነው። በዳንኤል 7:19 ላይ "እንግዲህ ዳንኤል ሆይ ያየኸውን ራእይ መርምር" ተብሎ የተነገረው፣ ያየነውን ራእይ እጅግ መመርመር አስፈላጊ እንደ ሆነ ሊያስገነዝበን ነው። እግዚአብሔር አንዳንዴ የሚሰጠን ራእይ ከሩቅ እንደሚታይ ሥዕል፣ ወይም ቅርጽ፣ በብዥታ የምንገነዘበው ዓይነት ነው። ከራእይ መመርመር ማነስ የተነሳ፣ በብዥታ እንደተረዳነው፣ እንዳለ በብዥታ ስንተረጉመው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኖ ይገኛል። እግዚአብሔር የሚሰጠንን ራእይ በሚገባ መርምረን ስንገነዘብ፣ የአሠራሩን ቅደም ተከተል፣ የአፈጻጸሙን የደረጃ በደረጃ ክንዋኔ፣ በቅጡ እናስተውላለን። ይኼ የአሠራሩን ቅደም ተከተል ሳናዛባ፣ የአፈጻጸሙን ደረጃ በደረጃ ሳናፋልስ በተግባር ለመተርጎምና፣ በውጤቱም ለእግዚአብሔር መንግሥት መሥፋት ለሰዎችም በረከት እንዲሆን ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

## 7▸ የራእይን ጊዜ መጠበቅ።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ራእይን ሲሰጥ ልክ እንደ ጉም መያዣና መጨበጫ በሌለው ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ይህ ነው ምስሉ፣ ቅርጹ ይህንን ይመስላል ማለት በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ይተወናል። ይኼኔ ያንን እጅና እግሩ ያልለየውን የራእይ ምስል ተግባራዊ ካላደረግኩ በማለት ራሳችንን ለችግርና ለስህተት ከመጋለጣችን በፊት፣ አስቀድመን ጊዜ ወስደን የተመለከትነውን ሰማያዊ ራእይ መመርመር ይገባናል። ምናልባት የተመለከትነው ብዥ ያለብን ራእይ፣ ለዋናው የራእይ አካል መግቢያ ይሆን ዘንድ ያቀረበልን ምልክት ሊሆን ይችላል። አንድን መጽሐፍ ይዘቱን፣ ብስለቱን፣ መልእክቱን ለመገምገምና ውሳኔ ለመስጠት በቅድሚያ



ከሽፋኑ ባሻገር፣ እያንዳንዱን ገጽ ማንበብ ይኖርብናል። እንደዚሁም ሁሉ ራእይን ልክ እንደ ጉም፣ በምንም ዓይነት የማይገባንን ምስል ይዞ ከተመለከትነው ጊዜ በመስጠት፣ የሚለጥቀውን የራእይ ንጋት መጠበቅ ይኖርብናል። ይህንንም ሲያደርግ እግዚአብሔር ዓላማ አለው። እግዚአብሔር ራእይን እንደ ንጋት እያደር እያጠራና እያፈካ ወስዶ፣ እንደ ቀን ብርሃን ቁልጭ የሚያደርገው የጊዜን ሂደትና ዝግመት ተጠቅሞ ነው። "የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፣ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል።" (ምሳሌ 4:18) ምክንያቱም የሚያሳየንን ራእይ ቁልጭ አድርጎ እስከሚገባን የሚያቆየው፣ ራእዩ እንዲፈጸምና ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈልግበትን የራሱን ሰዓትና የቀጠረውን ጊዜ ሲያመቻች ነው። ስለዚህ የተገለጠልንን ራእይ እንደ ጉም ብዥ ባለብን ሰዓት ተግባራዊ ለማድረግ መጣር ማለት በእግዚአብሔር ጊዜ ሳይሆን በራሳችን በሥጋ ውሳኔያችን የቀጠርነው ሰዓት ስለሆነ ውጤቱም ሥጋዊ ከመሆን አያልፍም። ይልቅ የእግዚአብሔርን ሰዓት ጠብቀን፣ የራእዩ ምንነት ቁልጭ ብሎ ታይቶን ተረድተን እስክምንገነዘብ ጊዜ ድረስ መጠበቅ መቻል አለብን።

ራእይ በእናቶች ማኅፀን ውስጥ እንደሚፈጠር ጨቅላን ሊመስል ይችላል። ጨቅላው ምንም እንኳ የተፀነሰ ቢሆንም፣ ደረጃ በደረጃ እያንዳንዱን ሰብዓዊ አካል ማግኘት የሚችለው በጊዜ ሂደት ውስጥ ነው። ወዲያው እንደ ተፀነሰ እጅና እግር፣ አፍንጫና አይን የመሳሰሉትም ብልቶች ተለይተው አኖሩትም። ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከቆይታ ወደ ቆይታ፣ ከእድገት ወደ እድገት እየተሸጋገረ ነው ማንነቱ ግልጽ ሆኖ የሚታየው። እንግዲህ ይህ ጨቅላ ከፅንሱ አንስቶ የእናቱን ማኅፀን በመልቀቅ እንደ ማንኛውም ሰብዓዊ አካል በምድር ለመመላለስ፣ እስከ ዘጠኝ ወር ጊዜ ይፈጅበታል። ታዲያ አባትየው ልጅ አገኘሁ ብሎ ገና ለገና ጨቅላው በሦስት ወር ላይ እንዳለ ካልተወለደ ብሎ ማስቸገር አይችልም፤ እናቲቱም ልጅ ፀንሻለሁ ብላ ገና በሽልነቱ

እያለ አገላግሎቱኝና አሳቅፉኝ ጡቴንም ሳጥባው በማለት ማንንም መጠየቅና ማስጨነቅ አትችልም። እርግጥ ነው ልጅ እርግዛለች። ግን እድገቱን ጠብቆ፣ የተቀጠረለትን ጊዜ አክትሞ (ጨርሶ) በጤንነት እስከምትገላገል ድረስ በትዕግስት የመጠበቁ ፋንታ የእርሷ ነው። ራእይም አንዳንዴ እንዲሁ ነው፤ የተመለከትነው ራእይ መፈጸም ያለበትን ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ማወቅ ይኖርብናል። የአፈጻጸሙንም ሁኔታ በቅደም ተከተል ለመገንዘብ የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅና ለእግዚአብሔር ቀጠሮ ቅድሚያ መስጠትን መማር ይኖርብናል። ብዙውን ጊዜ ይህን ዓይነቱን አሠራር ግምት ባለመስጠት ከፍተኛ ስህተት ውስጥ ወድቀው የሚገኙት ወጣቶች ናቸው። ወጣቶች ራእዩ ገና እንደታያቸው፣ ቅርጹንና ይዘቱን ሳይለዩ፤ እንደው በብዥታ ውስጥ እያሉ ተግባራዊ ካልሆነ ብለው ላይ ታች ሲሉ ይታያሉ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የሰጣቸው ራእይ፣ ከትዕግስትና ከግንዛቤ ማጣት የተነሳ ገና በእንጭጭነቱ እንዲቀጭ ይሆናል።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አመጣጥ እንኳ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር "ጊዜው በደረሰ ጊዜ ተወለደ" ነው ያለው። ምክንያቱም ያለ እግዚአብሔር ጊዜ የሚሆን ነገር የለም። በተለይ በአገልግሎታችን ውስጥ አዎንታዊ /positive/ ውጤት ማየት የምንችለው አገልግሎታችን ለእግዚአብሔር ጊዜና ቀጠሮ ሲገዛ ብቻ ነው። ቢሆንም በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንዳንድ አገልጋዮች ላይ የሕጻናት ባሕርይ ነው ጎልቶ የሚታየው። ሕፃናት ነገ ወይንም በሚቀጥለው ሳምንት ይደረግላችኋል ተብሎ ተስፋ ለተገባላቸው ቃል እምብዛም እመኔታ የላቸውም። አሁኑኑ ዛሬውኑ ካልተደረገ ወይንም ካላደረግኩ ማለት ይቀናቸዋል። ወጣቶች ራእይ የላቸውም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው ይሻልና፣ ራእይን ይሰጣቸዋል። ቢሆንም ያንን ራእይ ምግባራዊ ያደርጉበት ዘንድ፣ የአፈጻጸሙን ቅደም ተከተል የሚያስታውቃቸው በጊዜ ብዛት ሂደት ውስጥ ነው። አለበለዚያ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተከበረ ራእይ አለ አግባብ በመተርጎም፣ በአላዋቂነት በመፈጸም ያበላሹታል። የዚህ ችግር ተጠቂ



የሆኑት ወጣቶች የታላላቆቻቸውን ምክር የቆይታ ጥያቄ እንደ ጉዳትና እንደ ንቀት ሊቆጥሩት አይገባም። ራእይ ጊዜና ዘመን ስላለው በጊዜውና በዘመኑ እንደሚፈጸም መረዳት አለባቸው። ራእይ በተሰጠን ጀምበር ክዋኔን አያገኝም። ይህን ሁሉ ምስጢር የምንረዳው:- ታላላቆች ከሚለግሱን ምክር ስለሆነ፣ ምክራቸውን በሚገባ በልቦናችን በማዳመጥ በትዕግስት የእምላክን ጊዜ መጠበቅ መቻል አለብን። ካልቻልን ግን ገና ብዙ ይቀረናልና መቆየታችን ምንም አማራጭ የማይገኝለት ነው። ለነቢዩ ዕንባቆም እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን እውነት አስረግጦ ነው። ይኸውም "ራእዩ ገና እስከ ተወሰነ ጊዜ ነው፣ ወደ ፍጻሜውም ይቸኩላል፣ እርሱም አይዋሽም፤ ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፤ እርሱ አይዘገይም።" (ዕባ. 2:3) በማለት ነው እግዚአብሔር ዕንባቆምን ያረጋጋው።

ከሌላ አንጻር ደግሞ ራእይን እንደ ቋንጣ ዘልዝለው ለታይታ የሚሰቅሉም ጥቂቶች አይደሉም። እግዚአብሔር ራእይን የሚሰጠው ለዘመኑና ለጊዜው ችግር መፍትሔ እንዲሆን ነው። አንዳንድ ጊዜ በአገልግሎት ውስጥ የቆዩ ሰዎች የተለማመዱት ነገር እንዲነካባቸው ስለማይፈልጉ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠውን ራእይ በሥራ ላለመተርጎም የማይሰጡት ምክንያት የለም። በራሳቸው ፍርሃትና ጥርጥር ምክንያት ለዛሬ እራት የተሰጠውን ሥጋ ለነገ ቁርስ ወይንም ለወደ ፊት ምሳ እያሉ ዘልዝለው ይሰቅሉታል። ከዚህ የተነሳ የእግዚአብሔር ራእይ ቋንጣ ሆኖ ተሰቅሎ ጭስና አቧራ እየጠጣ ደርቆ ጣእሙን ከማጣቱም በላይ መልኩን ይቀይራል። በተለይም እንደዚህ ዓይነት አሠራር የሚያጠቃቸው በአገልግሎት ውስጥ ተመቻችተው ብዙ ጊዜ የቆዩት ናቸው። እግዚአብሔር ለወጣቱ ትውልድ የሚሰጠውን ራእይ ጸልየው በትክክለኛው ሰዓት የሚያውሉበትን ሃሳብ ከመስጠት ይልቅ በቆይታ ይይዙታል። ካልሆነም በሥራ ላይ ማዋል የማይቻልበትን ምክንያቶች ከራሳቸው ልምምድ ዝርዝር በመስጠት በማለት በመጣው ወጣት ራእይ ላይ ቀዝቃዛ ውኃ የሚያፈሱበት ጊዜ ይበዛል።

ይህ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል። ካልሆነ

ንጉሥ ሳዖልን በስብከታችን ጊዜ እየወቀስን በሕይወታችን እግዚአብሔር የጠራውን ዳዊት በዘመኑ እምላኩን እንዳያገለግል እንቅፋት ልንሆንበት እንችላለን። እንግዲህ ራእይን የምንፈትነው ከእግዚአብሔር መሆኑን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጊዜ የመጣ መሆኑን ጭምር ነው። ያለ ጊዜው እንዲወለድ የተደረገ ራእይ እንደሚሞት ሁሉ ጊዜ ያለፈበት ራእይም ስለሚደርቅ አይጠቅምም። ይህ እንዳይሆን ዘመኑን መለየትና ጊዜውን ማወቅ እንደ ይሳኮር ልጆች ጥበበኞች ያሰኛል። “እስራኤልም የሚገባውን ያደርግ ዘንድ ዘመኑን የሚያውቁ ጥበበኞች ሰዎች የይሳኮር ልጆች አለቆች ሁለት መቶ ነበሩ፤” (1ዜና. 12:32)



# ምዕራፍ አሥር
# የእግዚአብሔርን ራእይ ማስተዋል



# ም ዕ ራ ፍ  አ ሥ ር

## የ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ን  ራ እ ይ  ማ ስ ተ ዋ ል

“አይኖችህ ንጉሡን በውበቱ ያዩታል፤ እነርሱም በሩቅ ያለች ምድርን ያዩአታል።” (ኢሳ. 33:17)

የእግዚአብሔርን ራእይ ማስተዋል በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የእግዚአብሔርን ራእይ ለምን ማስተዋል እንደሚገባና ጠቀሜታውንም ጭምር ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን።

### እግዚአብሔርን ማየት

እግዚአብሔርን ማየት የራእይ መጀመሪያ ደረጃ ነው። በመሠረቱ ራእይ የሚጀምረው ራሳችንን ውስጣችንን በመመልከት ሳይሆን፣ ራሳችንን አቅንተን ወደ ላይ በመመልከት ነው። ለዚህም ነው በባለራእይነቱ የታወቀው ዳንኤል “ዓይኖቼን ወደ ላይ አቀናሁ” ሲል የሚሰማው። ራእይ በአጠቃላይ አነጋገር እግዚአብሔርን ማየት፣ ወደ እግዚአብሔር መመልከት፣ ወደ እርያም ማቅናት፣ ወደ መለኮታዊ ዙፋን ማስተዋል ማለት ነው። የእውነተኛ ራእይ ሁሉ መነሻው ከእርያም ነውና። ሕዝቅኤል ስለ ራሱ ሲመሰክር “በሠላሳኛው ዓመት በአራተኛው ወር ከወሩም በአምስተኛው ቀን በኮቦር ወንዝ በምርኮኞች መካከል ሳለሁ ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሔርንም ራእይ አየሁ።” ያለው ይህንኑ ለመግለጥ ነበር። (ሕዝቅ. 1:1) ። እስጢፋኖስ “መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና:- እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር



ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።” (ሐዋ. 7:55) ይላል። ሐዋርያው ዮሐንስም “ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንደዚህም አለኝ አትፍራ... ” (ራእይ 1:17) ሲል ይመሰክራል። ስለዚህ ራእይ የሚጀምረው አገልግሎትን በማየት፣ ወይም እግዚአብሔር የሚፈልገውን በማየት ሳይሆን፣ በቀጥታ እግዚአብሔርን በማየት ነው። ምንጩ እርሱ ነውና። በቅድሚያ መፈለግ ያለብን የእግዚአብሔር ፊት እንጂ ራእይን መሆን የለበትም። እግዚአብሔርን ለማወቅ እንጂ ከዚያ በፊት ራእይን እንድናገኝ መጸለይ አግባብ ያለው ጸሎት አይሆንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሃሳቡን መግለጽ የሚጀምረው እርሱን በማወቅ ውስጥ ስለሆነ፣ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ለማወቅ መጓጓት ይኖርብናል።

እግዚአብሔርን ስንፈልግ፣ በዚያ ጽኑ መሻታችን ውስጥ ፈቃዱንም ይገልጽልናል። አብርሃም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። አብርሃም ሰዶምና ገሞራን ከማየቱ በፊት እግዚአብሔርን አየ። እግዚአብሔር እንደ ወዳጅ የልቡን ሃሳብ ነገረው። እርሱም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ቆመ።

#### 1▸ እግዚአብሔርን በክብሩና በኃይሉ ማየት።

በመጀመሪያ ደረጃ አሁንም ተደግሞ መጠቀስ የሚገባው ሰማያዊ ራእይን ለማስተዋል እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ ክብርና ኃይሉ ማየት ይገባል። እግዚአብሔር እንደሚያይ እናይ ዘንድ እርሱ በሕይወታችን ቅድሚያ እንዲይዝ ይገባል።

አርአያነታቸውን ልንከተል የሚገቡን ታላላቅ የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን ባለ ራእዮች በመጀመሪያ ያዩት ሥራቸውን ወይም ራሳቸውን ወይም አካባቢያቸውን ወይም መሪዎቻቸውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው። ለምሳሌ ታላቁ የብሉይ ኪዳን ባለ ራእይ ኢሳይያስ “ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ተቀምጦ አየሁት ሲል የራእዩን አሃዱ ይጀምራል።” ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በታላቅ ዙፋን

ተቀምጦ አየሁት ብቻ ብሎ አያበቃም፤ ምድርም በእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ አየሁዋት፤ ሲል ይቀጥላል። ከዚህ የኢሳይያስ ራእይ ትልቅ ምስጢር እንረዳለን። ይኸውም እግዚአብሔርን የማያዩ፣ ወይንም የማየቱ ፍላጎቱም ሆነ ዝንባሌውም የሌላቸው ሰዎች ምድርን የሚመለከቷት በእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ ሳይሆን፤ ችግሯን ሰቆቃዋንና ብልሽቷን ብቻ ነው። እግዚአብሔርን የሚያዩ ግን በዚያ ውስጥ የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ይታደላሉ። በዚህም ምክንያት ለሰዎች ልጆች መፍትሄን ያመጣሉ። በሥጋ ነገሮችን ስንመለከት መፍትሄ የማይገኝለት ችግርን ነው የምናየው። በመንፈስ ወገኖቻችንን ስናይ ግን በውስጣቸው ኢየሱስን ስለምንመለከት፣ ያልጠበቅነው ውበትና የአምላክን ክብር እናያለን፤ እናይባቸዋለንም።

በኢሳይያስ ራእይ ውስጥ የምናጤነው ሌላ ምስጢር አለ። እግዚአብሔር በታላቅ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ከማየቱ በፊት ንጉሥ ዖዝያን አስቀድሞ መሞት ነበረበት። ዛሬም ቢሆን ለኛ ይህ ምስጢር በሕይወታችን ትልቅ የተምሳሌትነት ባሕርይ አለው። ምክንያቱም እኛ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ራእይ እንዳንመለከት የሚያደርጉን፤ በውሳጣችን ያሉት ንጉሥ ዖዝያኖች ባለመሞታቸው ነው፣ ንጉሥ ዖዝያን በሕይወታችን ብዙ ነገሮችን ይወክል ዘንድ የተቀመጠ እኩይ ተምሳሌት ነው። ይኸውም ንጉሥ ዖዝያን በትዕቢት የተሞላ ንጉሥ ነበር። እግዚአብሔር ከልጅነቱ መርጦ ቢያነግሠውም፤ ዙፋንና እድሜ በበረከት ቢሰጠውም፤ ወደ መጨረሻው ላይ ግን በእግዚአብሔር ላይ የድፍረት ኃጢአትን መሥራት ጀመረ። እንዲያውም፤ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በለምጽ በሽታ መታው። በእርሱ ዘመነ መንግሥት እስራኤል ከወራሪ ኃይላት ሁሉ ተጠብቀው በሰላም ስለኖሩ፣ እግዚአብሔርን መፈለግ ትተው በተዝናና ሕይወት ውስጥ ጭልጥ ብለው ገቡ። ወርቅና ብራቸው ዝገት፣ ወይን ጠጃቸው ከውኃ ጋር የተቀላቀለ ቅድስናቸው የረከሰ ሆነው ተገኙ። ስለዚህ ኢሳይያስ “ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።” (ኢሳ. 1:18)



የሚለውን የእግዚአብሔርን መልእክት ይዞላቸው ከተፍ አለ። ዖዝያን በሞተ ጊዜ ነቢዩም ዓይኑን ወደ ሰማይ አቀና እግዚአብሔርንም አየ።

ሙሴ እስራኤላውያንን በመምራት አገልግሎት ላይ እያለ፤ እስከ ዛሬ የምንደነቅባቸውን የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚያሳዩትን፣ ድንቆችና ተአምራቶችን ከተመለከተ በኋላ የመጨረሻውና ትልቁ ጥያቄ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበው “አንድ ጊዜ ብቻ ክብርህን አሳየኝና ያ ይበቃኛል” የሚለውን መሻቱን ነበር። ያም ማለት “እግዚአብሔር ሆይ ላይህ እፈልጋለሁ፤ ተጠምቼሃለሁ” ማለቱ ነው። ያገለገለው አገልግሎት፣ በአገልግሎቱም ውስጥ ያያቸው ድንቅና ተአምራቶች፣ የእግዚአብሔርን ክብር ማየትን እንደማይተኩለት ተገንዝቧል። ማገልገል፤ ድንቅና ተአምር ማየትና፣ የእግዚአብሔርን ክብር ማየት፣ በትይዩ የሚሄዱ እንጂ፣ አንዱ አንዱን የሚተኩ ልምምዶች አይደሉም።

እግዚአብሔር ከምሕረቱ ብዛት የተነሳ ቢጠቀምብንና ብናገለግለው፣ እግዚአብሔርን በሙሉ ክብሩ አየነው ማለት አይደለም። ለግል ሕይወታችን ግን በጽኑ መሻትና ፍላጎት የእግዚአብሔርን ክብር መጠማትና ማየት እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ ነው።

ያዕቆብ እግዚአብሔርን ለማየት ካለው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ሌሊቱን በሙሉ ሲታገል አደረ። እግዚአብሔርም ጥማቱን ቻል ሊልበት ስላልፈለገ ራሱን ገለጠለት፤ ያኔ ታዲያ ያዕቆብም በሐሴት “እግዚአብሔርን አየሁት ሰውነቴም ድና ቀረች።” አለ። (ዘፍ. 32:30)

### 2▸ እግዚአብሔርን በውበቱ ማየት።

በሁለተኛ ደረጃ የእግዚአብሔርን ራእይ ለማስተዋል፣ የእግዚአብሔርን የንጉሡን ውበት ማየት መቻል አለብን። (ኢሳ. 33:17) እውነተኛ ራእይ የክርስቶስን ውበት ያሳየናል። የእግዚአብሔርን ሥራውን ከሰማንና ኃይሉን ካወቅን በኋላ ዓይኖቻችን

የንጉሡን ውበት ማየት አለባቸው። ይህም ማለት እግዚአብሔርን ለማየት አስቀድመን የክርስቶስ ኢየሱስን የመስቀሉን ሥራና ኃይል መረዳት አለብን ማለት ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔርን ከነውበቱ ለማየት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በውስጣችን መለማመድ አለብን። በአዲስ ኪዳን ቀዳሚ ሰማዕት በመሆን የታወቀው እስጢፋኖስ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከነሙሉ ክብሩና ውበቱ ያየው፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በውስጡ ከተገለጠ በኋላ ነው።

## እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት

እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት። ሌላው ማወቅ የሚገባን እግዚአብሔርን ካየንና በመሻታችንና በጸሎታችን ከተጣበቅን በኋላ፣ የሚቀጥለው ደረጃ እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት መጀመር ነው። ብዙዎች በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዚህ ልምምድ ውስጥ ለማለፍ እድል አግኝተዋል። በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ፊት በመሻታቸው፣ እግዚአብሔርም፣ ፈቃዱን ይገልጥላቸው ሃሳቡንና እቅዱን ያጫውታቸውና እርሱ የሚያየውን ያሳያቸው ዘንድ በመንፈስ ወደ እርሱ ይማርካቸዋል።

እንግዲህ በአግባቡ ራእይ ብለን የምንሰይመው እርሱን ነው። ዓይኖቻችን አስቀድመው እግዚአብሔርን ያያሉ፤ ቀጥለውም የእግዚአብሔርን ዓይን ተከትለው፣ እርሱ የሚያየውን ይመለከታሉ። ከዚህ ዓይነት የአሠራር ቅደም ተከተል ውጭ፣ ሰማያዊ ራእይን መጠበቅ ራስን መደለል ይሆናል። የሚያየውን ሳናይ፣ የሚታየውን ማየት አንችልም። የነቢያትና የባለ ራእዮች ሕይወትና አገልግሎት የተመሠረተው በዚህ ዓይነት የአሠራር ሥርዓት ነው። ለዚህም አብነት ይሆን ዘንድ የኤርምያስን የራእይ ልምምድ መጥቀስ ይቻላል። ኤርምያስ አስቀድሞ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ከተገናኘና ካየው በኋላ ማየት የሚገባውን ሊያሳየው ወደ አንድ ቦታ ወሰደው። ይህም ኤርምያስ በመጀመሪያ አምላኩን ካየ በኋላ ወደ ለጣቂው ደረጃ እየሄደ እንደ ሆነ ሲያመለክተን ነው። ምክንያቱም ኤርምያስ



እግዚአብሔርን ከማየቱ በፊት ማየት የሚገባውን አይደለም ያየው። ያማ ቢሆን የእግዚአብሔርን አሠራር ቅደም ተከተል ጥሷል ባሰኘው ነበር። እውነተኛውን ራእይንም ባላየም ነበር። የኤርምያስን የራእይ ልምምድ በትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 1 ላይ በዝርዝር ማየት ይቻላል። ግን ይበልጥ አጽንኦት ለመስጠት በኤርምያስ ምዕራፍ 1:11-12 ላይ እግዚአብሔር ለኤርምያስ ያቀረበውን ጥያቄ እናገኛለን። እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት በተለያየ መንገድ መተርጎምና መበየን እንችላለን። ለምሳሌ በቁጥር 11 ላይ "ኤርምያስ ሆይ! ምን ታያለህ?" የሚለው ጥያቄው "ለመሆኑ እኔ የማየውን ነው ወይስ ሌላ ነው የምታየው?" የሚል ይመስላል። ለአሞጽም የቀረበው እንደዚሁ ዓይነት ጥያቄ እንደ ነበረ ቃሉ ሲመሰክር እንዲህ ይላል:- "እግዚአብሔርም አሞጽ ሆይ የምታየው ምንድር ነው? አለኝ።" (አሞጽ 7:8) እኛም ራእይን ስንቀበል፤ የእግዚአብሔርን ዓይን ተከትለን እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት መቻል አለብን እግዚአብሔር በሰማይ ነውና፣ እንደ ገና ወደ ሰማይ አቅንቶ አያይም። ራሱን ወደ ታች አዘንብሎ የሚመለከተው በምድር ያለውን ነው። "እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና።" (2ዜና 16:9) ለሰው ልጆች ያለውን ሃሳብ፣ ዓላማና እቅድ ነው የሚያየው። እርሱ "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።" (ኤር. 29:11) የሚለው ለዚህ ነው። ባለራእዮችና ነቢያት አስቀድመው እግዚአብሔርን ካዩ በኋላ፣ ከዚያም የእግዚአብሔርን ዓይን ተከትለው በእግዚአብሔር ሃሳብና እቅድ መሠረት ወደ ምድር ሲመለከቱ ታላቅ ሸክም ይሰማቸዋል። ለዚህም ነው የአብዛኛዎቹ ነቢያት የአገልግሎት ምዕራፍ በሸክም የሚከፈተው። ለምሳሌ ያህል "ነቢዩ ዕንባቆም ያየው ይህ ነው።" (ዕንባ. 1:1) "በሚልክያስ እጅ ለእስራኤል የሆነ የእግዚአብሔር ሸክም ይህ ነው።" (ሚልክ. 1:1) ነቢያቱ የአገልግሎት ሕይወታቸውም

በአንባና በእዬዬ የሚታጀበው እግዚአብሔር የሚያየውን የምድርን ጉስቁልና እነርሱም አይተዋልና ነው። ብዙውን ጊዜ ለተራው ሕዝብ በማይገባው መንገድ የሰቆቃን ሕይወት ሲመሩ ይታያሉ። የኤርምያስ የልቅሶ መልእክት ሰቆቃወ ኤርምያስ በመባል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተገልጧል። ኤርምያስ ለምን እንደሚያነባ ቢጠየቅ መልሱ፤ "እኔ የማነባበት ምክንያት እግዚአብሔር የሚያየውን ስላየሁ ነው።" ሳይል አይቀርም። "ሰቆቃወ ኤርምያስን" በጥሞና መመልከት ይህን ነገር ግልጽ ያደርገዋል። ስለዚህም ነው እርሱ እንኳ ባይወድ፣ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር የሚያየውን አይቷልና፣ በውስጡ እንደ ፍም እያቃጠለው፣ ራእዩን ተቀብሎ መልእክቱን ለማስተላለፍ የወሰነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን አስተውል።

## እግዚአብሔር እንደሚያየው ማየት

ለባለ ራእዮችና ለነቢያት አስተውሎት እግዚአብሔር እንደሚያይ ማየት እጅግ ወሳኝ ነው። ይኸውም ከዚህ በፊት በሚገኙት ደረጃዎች መሠረት፣ በቅድሚያ እግዚአብሔርን አይተው፣ ቀጥለውም እግዚአብሔር የሚያየውን አይተው ከዚያ ደረጃ በኋላ ተሳስተው ለሃሰተኛ ነቢያትነት የተዳረጉ ብዙዎች ናቸው። ከዚህ በፊት የሚገኙትን ሁለቱን የራእይ ደረጃዎች ካለፉ በኋላ ሦስተኛው ደረጃ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ይኸውም እግዚአብሔር የሚያየውን ሲያዩ፣ እነዚህ ባለ ራእዮች ከምን አንጻር እንዳዩት ራሳቸውን መገምገም አለባቸው። ይህም ማለት ያዩትን ነገር፣ በእግዚአብሔር አንጻር፣ በእግዚአብሔር ምልከታና በእግዚአብሔር እይታ አይተዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ ለራእያቸው ሰማያዊነት ወሳኝነት ስላለው ነው። ለመሆኑ እግዚአብሔር አይቶ ልቡ እንደ ከበደበት ሁሉ እነሱንም ከእይታቸው በኋላ ልባቸውን አክብዶባቸዋል ወይ? ለራእያቸው እውነተኛነት እግዚአብሔር አይቶ ልቡን ያስደሰተውን ያህል እነርሱም በእርሱ አንጻር ተመልክተው ልባቸው ደስ ተሰኝቷል ወይ? የሚሉት



ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለባቸው።

ለመሆኑ እግዚአብሔር እንደሚያይ ማየት ማለት ምን ማለት ነው? ይህንን ጥያቄ ግልጽ ለማድረግ የሚከተሉ ነጥቦችን፣ በመዘርዘር መመልከት እንችላለን። ይኸውም፣

### 1▸ ራስን በእግዚአብሔር ዓይን ማየት።

የእግዚአብሔርን ራእይ ለማስተዋል እራስን ማየት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ራሱን ከነክብሩና ከነውበቱ ካሳየን በኋላ ቀጥሎ ራሳችንን እንድናይ ነው የሚያደርገን። በኢሳይያስ ሕይወት ውስጥም የተከናወነው ይኸው ልምምድ ነው። ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔርን በታላቅ ዙፋኑ ላይ ሆኖ ካየው በኋላ ወዲያውኑ ራሱን ነው የተመለከተው። ያኔ ታዲያ የራሱን ኢምንትነት ተረድቶ "ወዮልኝ" በማለት እዬዬውን ቀጠለ። ጳውሎስም በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ ኢየሱስን ካየ በኋላ ተመልሶ የተመለከተው ራሱን ነው፤ ከዚያ በኋላ የራሱን ደካማነት ተገንዝቦ ንስሐ ገብቶ "ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?" በማለት ገበርኩ በማለት ራሱን ለጌታ አንበረከከ።

### 2▸ ሌሎችን ማየት።

እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመለከታቸው በፍቅር ዓይንና በርኅራኄ ነው። ጥሪውም ለምሕረትና ለይቅርታ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳየናል። እንግዲህ ከጌታ ራእይን የተቀበለ አገልጋይም ሌሎችን ሲመለከት በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ርኅራኄ፣ ይቅርታና ምሕረት በመመልከት ማገልገል፣ ማበረታታት፣ ማጽናናትና ወደ እግዚአብሔር ተስፋ መጥራት ይኖርበታል። የእግዚአብሔርን ነቢያቶች ባለ ራእዮች ያሰኛቸው እግዚአብሔርን ማየታቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚያየውን አይተው ለሌሎች የርኅራኄን እንባ ማንባታቸው ነው። የኤርምያስ ሕይወት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። (ሰቆቃወ ኤርምያስን ይመልከቱ)

### 3▸ ነገሮችን ከታሪክ አንጻር ማየት።

የእግዚአብሔርን ራእይ ለማስተዋል እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት መቻል አለብን። ይህም ማለት በራእይ ቁጥር 1:19 ላይ የተጻፈውን ማጤን አለብን ማለት ነው። “እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።” ከዚህም እውነት ውስጥ ሦስት ነገሮችን መዝዘን ማውጣት እንችላለን። እነዚህም ነገሮች ራእዩን ተጨባጭና እውነተኛ ለማድረግ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

**3•1▸** ያለፈውን ማየት:- ራእይ ያለፈውን ነገር እንድንረዳ ያደርጋል። እግዚአብሔር የሚሰጠን መገለጥ ታሪክን እንድንረዳ ያደርገናል። ያለፈው ነገር ለምን ተደረገ? የሆነው ነገር ለምን ሆነ? ተብሎ ለሚነሳው ጥያቄ እግዚአብሔር የሚሰጠው መገለጥ መልስ ነው። እግዚአብሔር የሚሰጠን መገለጥ፣ እግዚአብሔር በውስጣችን የሚያሰርጸው መረዳት፣ እግዚአብሔር በውስጣችን የሚያኖረው ጥበብ ታሪክን ለመገንዘብ፣ ለመተርጎምና ለመበየን እጅግ አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ ነገራትን ከታሪክ ጋር ማገናዘብና ማዛመድ እጅግ ይጠቅማል። ምክንያቱም ያለፈውን መረዳት አለብንና ነው። የዘመናችን ሰዎች የታሪክ ፍሬዎች ናቸው ይባላል። ምክንያቱም ታሪክ በሰዎች ቅብብሎሽ ተረማምዶ ነው እዚህ የደረሰው። ስለዚህ ታሪክ የዛሬን ሁኔታ መግለጫ መዝገበ ቃላት ነው።

**3•2▸** የአሁኑን ማየት:- እውነተኛ ራእይ ባለፈው ሁኔታ ወይንም ታሪክ ላይ ብቻ እንድናተኩር ሳይሆን የአሁኑንም ሁኔታ እንድናይ ያደርገናል። እግዚአብሔር የሚያየው እንደዚህ ነውና። በዮሐንስ ምዕራፍ አራት ላይ እንደምናገኘው፣ ጌታ ኢየሱስ “እናንተ ገና አዝመራው አልደረሰም ትላላችሁ ግን ዓይናችሁን አንሱ አዝመራው እንደ ደረሰ እዩ።” በማለት ሲያስገነዝብ እንመለከታለን። “ደርሷልና እዩ” ሲል የአሁኑን ጊዜ፣ የአሁኑን ሁኔታ፣ የአሁኑን ድርጊትና ክዋኔ ተመልከቱ ማለቱ ነው። እንግዲህ እውነተኛ ራእይ አለን ካልን ዘንዳ አሁን ያለውን ሁኔታ ማየት፣ መገንዘብና ማጤን ይገባናል። በታሪክ ብቻ ረክተንና



ተወስነን የምንቀመጥ ሰዎች መሆን የለብንም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ክንድ በታሪክ ብቻ ተወስኖና ተገድቦ የቆመ አይደለም። ዛሬም የሚሠራው፣ የሚያደርገው የሚፈጽመውና የሚያከናውነው ነገር አለው። ስለዚህ ዛሬ እግዚአብሔር የሚሠራውን ማየት መቻል አለብን። ምናልባትም በዚህ ዘመን ትልቁ ችግራችን ዛሬ እግዚአብሔር አምላካችን የሚሠራውን ማየት አለመቻል ነው። በወንድሜና በእህቴ በኩል እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በድርሻዬ ከማየት ይልቅ እኔ እጅግ እንደሚያስፈልግ ቅመም በሁሉም ቦታ ካልተገኘሁ ማለትን እንመርጣለን። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ሲሠራ ለማየት ለሚጓጓ ሕይወት ታላቅ እንቅፋትና ድክመት ነው።

**3•3▸** የወደፊቱን ማየት:- እውነተኛ ራእይ ያለፈውንና የአሁኑን በማየት የሚወሰን ሳይሆን የወደፊቱንም የማየት ችሎታ አለው። በመሠረቱ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሦስቱ ነገሮች እጅግ የተያያዙ ናቸው። የአሁኑን ለማየት፣ ያለፈውን መገንዘብና ማጤን ያስፈልጋል። የወደፊቱን ለመገንዘብ የአሁኑንና ያለፈውን መረዳት እጅግ የተገባ ነው። ራእይ አየን ስንል፣ ታሪክን ማየት አለብን፣ ዛሬን መመልከት አለብን፣ ነገን አርቀን መገንዘብ አለብን ማለት ነው። በትናንትና ታሪክ ተመሥርቶ፣ ዛሬን ተንተርሶ፣ ነገ እግዚአብሔር ምን እንድንሠራለት እንደ ፈለገ ማየትና መዘጋጀት ማለት ነው:- ራእይ። ይኼኔ ነው እውነተኛና የተሟላ ራእይ አየን ማለት የምንችለው።

**3•4▸** የእግዚአብሔርን ራእይ ለማስተዋል:- የእግዚአብሔርን አሠራር ማየት አለብን። መረዳትም አለብን። ይህንንም ስንል:-

በራእይ 1:12 ላይ እንደ ተመለከተው እግዚአብሔር የሚናገረንን ድምጽ ለማየት ዞር ማለት አለብን። የራእይ ምስጢር ዞር በማለት ላይ ነው ያለው። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ራእይ ሳይገባንና ሳይረዳን እንደ ጠጠረብንና እንቆቅልሽ እንደ ሆነብን የሚቆየው፣ ዞር ብለን እግዚአብሔር የሚሠራውን ከማየት ይልቅ አንዴ ራሳችንን ባመለከትንበት ብቻ ተወስነን ግትርና ድንድን ብለን ለመሄድ ስንሻ ነው። እግዚአብሔርም

ሲናገር ዞር ብለን ማየትና የመስማት ጊዜ አንሰጥም። በእኛ ብሶ እኔ ሃሳቤን ወስኛለሁ፣ እኔ በቀየስኩት ጎዳና ግትር እንዳልኩ እነጉዳለሁ፣ አንተ ግን አታስቸግረኝ ልንለው ይቃጣናል። በዚህ ምክንያት ጥፋታችንን ጥፋት ነው፣ በደላችንን እውነትም በደል ነው፣ ስህተታችንን እውነትም ስህተት ነው፣ ውድቀታችንን እውነትም ውድቀት ነው ብለን ተቀብለን ራሳችንን በንስሐ ለማረምና ለመመለስ ይከብደናል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ታላላቆች የሚመክሩንንና የሚያርሙንን ሁሉ በከማንእንሼ ስሜት ባለመቀበል ብዙ ጊዜ ፍሬ አልባ ለሆነ ሩጫ ራሳችንን አጋልጠን እንገኛለን። በመሠረቱ አንገትን ማደንደን ለእስራኤላውያን እንኳ አልበጃቸውም። የእግዚአብሔርም ቃል "ብዙ ጊዜ ተዘልፎ አንገቱን ያደነደነ ድንገት ይሰበራል። (ምሳሌ 29:1) ሲል ይህንኑ እውነት አጽንኦት ለመስጠት ነው። የእግዚአብሔርን አሠራር ለማየት ዞር ማለት፣ እግዚአብሔር ወደሚያዞረን አቅጣጫ በታዛዥነትና በሙሉ ፍላጎት ለመዞር ፈቃደኞች መሆን አለብን። ያኔ ነው እንግዲህ በራእያችን ውስጥ የእግዚአብሔርን አሠራር ለማየትና ለመለማመድ የምንችለው።

ዘወር በማለት የምናያቸው ነገሮች አሉ። ይኸውም በመጀመሪያ የምናያት ቤተ ክርስቲያንን ነው። በራእይ 1:12 ላይ የምናገኘው ትዕይንት ይህንን እውነት የሚያጎላልን ነው። "የሚናገረኝንም ድምጽ ለማየት ዘወር አልሁ፤ ዘወርም ብዬ ሰባት የወርቅ መቅረዞች አየሁ፣" ዮሐንስ በራእዩ ወቅት ዞር ብሎ የተመለከተው እነዚያን ሰባት የወርቅ መቅረዞች ነው። እነዚያ ሰባት የወርቅ መቅረዞች አብያተ ክርስቲያናትን ይወክሉ ዘንድ የተቀመጡ ተምሳሌቶች ናቸው። በራእይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ላይ ዘልቀን ስንመለከት እነዚያ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ከነድካማቸው፣ ከነፈተናቸው፣ ከነማንነታቸው ቁልጭ ብለው ተገልጸው እናገኛቸዋለን። እግዚአብሔር ራእይን ሲያሳየን በተለይም፣ እርሱ የሰጠንን መገለጥ ስናስተውል ዘወር አድርጎ የሚያሳየን ቤተ ክርስቲያንን በፍጹምነቷ ምሉዕ የሆነች፣ አገልግሎትዋ ምንም ፈተና የሌለበት የደስታና



የፈንጠዝያ አዳራሽ፣ ክርስትናንም እጅግ አመቺ ጎዳና አድርጎ አይደለም። እርሱ ይዋሽና ይደልል ዘንድ ሰው አይደለም። ስለዚህ ዘወር ብለን ስናይ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከነድካምዋና፣ የሚጠብቀንንም አገልግሎት የከበደና ታላቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ እንደ ሆነ ሳይደብቅ ይነግረናል። ዓይኖቻችንን ከፍቶ ቤተ ክርስቲያን ያላትን ደካማና ጠንካራ ጎን በገሃድ እንድንመለከት ያደርጋል።

ቀጥሎም እግዚአብሔር የሚያሳየንን ለማየት ዘወር በምንልበት ጊዜ መቅረዞችን ብቻ ሳይሆን በመቅረዞች መካከል የሚመላለሰውን የሰው ልጅንም እንድንመለከት ያደርጋል። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንን ድካምና ውድቀትን ብቻ አሳይቶ ተስፋ እንድንቆርጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። የቤተ ክርስቲያንን ውድቀት አይተን፣ መልስ ለዘላለም እስከ ዘላለም እንደ ጠፋበት ጎስቋላ ሰው፣ ዘመናችንን በእዬዬ እንድናሳልፍም አይፈልግም። ወድያውኑ፣ ለቤተ ክርስቲያን ድክመት ብርታት የሚሆናት፣ ለውድቀቷ ትንሣኤ የሚሆናት፣ ለጥያቄዋ መልስ የሚሆናት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያሳየናል።

ከዚያ በኋላ የንጉሡን፣ የረድኤታችንን ውበት እጅግ ጎልቶ እናየዋለን። ኃዘናችን በደስታ፣ ልቅሶአችን በሳቅ፣ ሰቆቃችን በመጽናናት፣ የኀዘን እንጉርጉሮአችን በውዳሴና በዝማሬ ይለወጣል። የንጉሡን ውበት መመስከር፣ የራሱን ታላቅነት መስበክ፣ ኃያልነቱን መናገር ረድኤትነቱን ማብሰር፣ መድኃኒትነቱን ማወጅ ይቀናናል። ምክንያቱም ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ፍጹም ለመሆን የማትችል፣ ደካማ ብትሆንም፣ በመሃከሏ እየተመላለሰ የሚያስተካክላት፣ ወደ ፍጹም ሙላት የሚያደርሳት ኢየሱስ ክርስቶስ ስላላት ነው። እርሱ በጉድለትዋ ሁሉ ሙላትዋ ነውና። "እርሱዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት።" (ኤፌ. 1:23) ከዚያም በላይ ጌታ ኢየሱስ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በድካምዋ እንዳትቀር ለራሱ እያነጻትና እየቀደሳት ለፍጹምነት እያዘጋጃት ነው። "...በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት

ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።" (ኤፌ. 5:26-27) ይህን ስለተገነዘበ ዮሐንስ በምዕራፍ ሁለትና ሦስት ውስጥ ከሁሉ ነገር በፊት ለሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አቀረበላቸው።

በጊዜው ዮሐንስ በራእዩ ውስጥ ከሁሉም በላይ የማረከው ኢየሱስ ክርስቶስ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በመመላለስ የተበላሸውን ማስተካከሉ ብቻ ሳይሆን፣ አፉን ያስያዘው፤ ያስደነቀው፤ ጉድ ያሰኘው የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ውበትና ግርማ ነው። ዘወር ብለን ጌታ ኢየሱስን ከሙሉ ውበቱና ከነግርማ ሞገሱ ስንመለከተው ያኔ ሁሉንም ነገር እንረሳለን። የኢየሱስን ግርማ ሞገስና ውበት አይቶ የሚመካና ቆሞ ራሱን የሚያኩራራ አይኖርምና። ዮሐንስ መጥምቁ እንዳለው "እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።" (ዮሐ. 3:30) ለማለትም እንገደዳለን። ምክንያቱም ያኔ ኢምንትና ታናሽ መሆናችንን እንረዳለንና። የክርስቶስ ውበት በውስጣችን ልዩ የሚያደርገው ነገር አለ። ኢየሱስን ስናይ ኢየሱስም ያየናል። ዮሐንስ በራእዩ እንደ ተመለከተው የኢየሱስ ዓይኖች እንደ እሳት ነበልባል ናቸውና የኢየሱስ እይታ እንደው በከንቱ ለማየት ብቻ የሚሆን ሳይሆን፣ በውስጣችንም የሚያከናውነው ነገር አለ። ይኸውም ነበልባል ዓይኖቹ ሲመለከቱን በውስጣችን መቅለጥ የሚገባቸውን ነገሮች በኃይሉና በብርታቱ ያቀልጣል፣ ያነጥረናልም። በዚያ እንደ እሳት በሚንቦለቦሉ ዓይኖች ፊት እኔነት፣ ሥጋዊ ፍላጎት፣ ኩራት፣ ትዕቢት፣ ዘረኝነት፣ ሌሎችንም ተሸክመን የምንዞራቸው ግሳንግሶች ሁሉ ጸንተው ለመቆየት አቅም የላቸውምና ይቀልጣሉ። ታድያ ይህ ሁሉ ይሆን ዘንድ አስቀድመን እኛ ዞር ብለን ፊቱን ማየት አለብን። ኢየሱስ ያየው ነገር ሁሉ የኢየሱስ ይሆናልና ማንነታችን ሁሉ ለእርሱ ይገዛል። እያንዳንዱ አካላችን እኛን ክዶ ለኢየሱስ ገበርኩ ይላል። ዮሐንስ በራእዩ ኢየሱስን



ዘወር ብሎ ካየ በኋላ፣ እንደ ሞተ ሰው ሆኖ ወደቀ፣ እግሮቹ እርሱን ታዘው ችለውት ሊቆሙ አልቻሉም፣ ከዱት፤ ምክንያቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ነበልባላዊ ዓይን ተመልክተዋቸዋልና።

## የ ክ ር ስ ቶ ስ ን ብ ቃ ት ማ የ ት

በአገልግሎታችን ውስጥ የክርስቶስን ውበት ማየት እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ያህል፣ የክርስቶስን ብቃትና ችሎታ መመልከት ደግሞ እጅግ አስፈላጊው ጉዳይ ነው። በአገልግሎታችን ብቃት እንዲኖረን የሚያደርገን እኛ በራሳችን ያለን ጥልቅ ማስተዋልና ጥበብ ሳይሆን፣ የክርስቶስን ችሎታና ብቃት ብቻ ማስተዋላችን ወይም መመልከታችን ነው። ለዚህም ነው ዮሐንስ በራእዩ የአብያተ ክርስቲያናትን ድካም በብቃቱ የሚሸፍነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ የተመለከተው። በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2ና 3 ውስጥ እንደምንመለከተው የአብያተ ክርስቲያናት ድካም ተዘርዝሮ ከተቀመጠና፣ ጆሮ ያለው ሁሉ ሰምቶ ልብ እንዲል አዋጅ ከተነገረ በኋላ፣ በዚያው አንጻር የእያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ድካም ለመሸፈንና መፍትሔ ለመስጠት ዮሐንስ ራእዩን የጀመረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ብቃቱን የሚገልጹትን ልዩ ባሕርዮችን ነቅሶ በማውጣትና በማሳወቅ ነው።

ለምሳሌ በምዕራፍ 2:1 ላይ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በተጻፈው መልእክት መግቢያ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ በሙላት የገለጸው እንዲህ ብሎ ነው። "በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው"። በተመሳሳይ ምዕራፍ ውስጥ በቁጥር 8 ላይ ደግሞ ስለ ሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ የተገለጸላት "ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው" ተብሎ ነው።

እንግዲህ በዚህ ሁሉ የዮሐንስን አገላለጽ እንደምንረዳው፣ ለባለ ራእዩ ዮሐንስ የአቢያተ ክርስቲያናትን ችግር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቁልጭ አድርጎ ካሳየው በኋላ፣ ለችግራቸውና ለድካማቸው መፍትሄ ብሎ

ያቀረበው የራሱን ግምት፣ ወይም የራሱን ጥበብ፣ እንዲሁም የራሱን ማስተዋል፣ ወይንም የራሱን ልምምድ አልነበረም። በየችግራቸው አንጻር መልስና መፍትሔ የሚሆናችውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቃት ብቻ ነው ያሳየው። ምክንያቱም ለሁሉም ችግር መፍትሔና መልስ ለመሆን ብቃት ያለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውና። ከዚህም ጋር መስተዋል ያለበት ቁም ነገር፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ለአብያተ ክርስቲያናቱ መፍትሔ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሳየት ከመሞከሩ በፊት አስቀድሞ እርሱ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በግሉ ማየት መረዳት መገንዘብና ማስተዋል እንደ ነበረበት ነው።

የሚከተለው ነጥብ፣ በተለይ እግዚአብሔርን ከተለያየ መስክና የአገልግሎት አቅጣጫ ፈልቅቆ አውጥቶ እርሱ አድርግ የሚላቸውን ብቻ እንዲፈጽሙ ከጌታ በር ለተከፈተላቸው ሰዎች በሚገባ ሊያጤኑትና ሊገነዘቡት የሚገባ ነጥብ ነው። ይህም ነጥብ ለአገልግሎት ቁልፍ የሆነ መክፈቻ ዋስትና ነው። በራእይ 1:18 ላይና በራእይ 3:7 ላይ የሚገኙት ጥቅሶች የዚህ ነጥብ መንደርደሪያ ጥቅሶች ናቸው። በራእይ 1:18 ላይ ያለው እንዲህ ይላል። "አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ። ሞቼም ነበርሁ፣ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ፣ ሕያው ነኝ። የሞትና የሲዖልም መክፈቻ አለኝ።" በራእይ 3:7 ላይም የተገለጸው እንዲህ ተብሎ ነው። "የዳዊት መክፈቻ ያለው፣ የሚከፍት የሚዘጋም የሌለ፣ የሚዘጋ የሚከፍትም የሌለ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው።" ይላል። ቀድሞ የክርስቶስን ውበት ከዚያም የእርሱን ብቃት አይተናል ተገንዝበናል። ግን አገልግሎታችን የክርስቶስን ውበትና ብቃት ብቻ በመመልከት ሊበቃው አይገባም። ከዚያም አልፎ መዝለቅ ይኖርበታል። ይኸውም ለአገልግሎታችን ዋስትናና መተማመኛ የሆነውን ቁልፉን ማየትና፣ በባለቁልፉ፣ በባለመክፈቻው ላይ ያለን እምነት ይበልጥ ሥር እንዲሰድና እንዲያድግ ያስፈልጋል። ቁልፉ በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ነው፤ ባለቤቱም እርሱው ነው።



በዚህ ተምሳሌታዊ አገላለጽ ውስጥ እጅግ ጥልቅ የሆኑ ሁለት ቁም ነገሮችን በሚገባ ማጤን ይኖርብናል። ይኸውም የመጀመሪያው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ጥያቄአዊ ዐረፍተ ነገር ቀርቧል። ለመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቁልፉን እርሱ ራሱ ከመያዝ ይልቅ፣ ለምን በአገልጋዮቹ ዘንድ አልተወም? ብለን ብንጠይቅ ብዙ እውነቶችን መረዳት እንችላለን። በመሠረቱ ቁልፉ በአገልጋዮች ዘንድ ቢሆን ኖሮ ብዙዎች የብዙዎችን አገልግሎትና ሕይወት ባበላሹ ነበር። ከዚያም በላይ ግን አገልጋዮች ቁልፉ በእጃቸው ቢገባ ኖሮ የቁልፉ ባለቤት የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማየት ፍላጎቱም ሆነ ዝንባሌውም ሊኖራቸው ባልቻለ ነበር። "ቁልፉ አንዴ በእጄ ገብቷልና ምን ያለማምጠኛል የሚለው የዕብሪት መንፈስ እያሌ ትጉህ አገልጋዮችን እንከባልሎ በጣለ ነበር። ሁልጊዜ ቁልፉ በባለቤቱና ብቃት ባለው ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ከሆነ ግን፣ ማንኛውም አገልጋይ፣ ሊያገለግል በተጠራበት የአገልግሎት ደጃፍ ቆሞ ይከፍትለት ዘንድ የጌታን ፊት የመሻትን፣ ኢየሱስን ደጅ የመጥናት ዕድልን ያገኛል። ብዙ ሕጻናት ሊገቡበት ወደሚፈልጉበት በር ደርሰው ተቆልፎ ሲያገኙት የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ ሙከራቸው የሚሆነው ቁልፉን በእጃቸው የያዙትን ወላጆቻቸውን ወይም ታላላቆቻቸውን ቀርበው ይከፍቱላቸው ዘንድ መጠየቅ ወይንም መለማመጥ ነው። የጌታና የአገልጋዮችም ቀረቤታ ልክ እንደዚሁ፣ የአባትና የልጅን ቀረቤታ የሚያጎላና የሚያንጸባርቅ ነው። ቁልፉ በልጆች እጅ ቢገባ፣ ይጠፋል፣ ለማይመለከተውና ለማይገባው ሰው በቸልተኝነት ይተላለፋል፤ ለሚገባውና ለሚመለከተው ሰው ይነፈጋል፤ በጠቅላላው የአሠራር ዝብርቅርቅነትና ብልሽት ይከተላል። ልክ እንደዚሁ ቁልፉ በአገልጋዮች ዘንድ ቢሆን ተመሳሳይ ብልሽት መከሰቱ የማይቀር ዕዳ ነው።

ስለዚህ በየትኛውም ጊዜ ቢሆን አንድ አገልጋይ ወደ ተመረጠበት የአገልግሎት ደጃፍ ቀርቦ ቢያንኳኳና በራሱ ኃይልና ብርታት ጥረት ቢያደርግ እንደማይሳካለት ሲገነዘብ፣ ያለው ብቸኛ መፍትሔ ዓይኖቹን ወደ ቁልፉ ባለቤት ማንሳትና ደጅ መጥናት ነው። በዚህ አስደናቂ ትዕይንት

ውስጥ ደግሞ እጅግ የሚማርክ ጥልቅ ምስጢር አለ። ይኸውም አገልጋዩ ደጆቹ ይከፈቱለት ዘንድ ቁልፉን በእጆቹ ወደ ያዘው ወደ ክርስቶስ ሲመለከት፣ ዓይኖቹ በቅጽበት ተስበው ትልቅ የመመሰጥ ስሜት አስቀድመው የሚፈጥሩበት ቁልፉ ወይንም ጣቶቹ ሳይሆኑ በቀራንዮ መስቀል ላይ በምስማር የተቸነከረባቸው የቁስሉ ምልክቶቹ ናቸው። በዚያን ሰዓት ያ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ከመጣደፉ በፊት በጌታ ፍቅር ልቡ ተነክቶ ደግሞ በፍቅር የተሞላ ኪዳኑን ያድስ ዘንድ ይሆናል።

ጌታም ልቡ በፍቅር የተነካውን አገልጋይ ደጆቹን ሲከፍትለት የሚለው ነገር አለው። “ልጄ ሆይ ይህን በር የምከፍትልህ ከፍቅሬ የተነሳ ነው። ስለዚህ በዚህ በምከፍትልህ በር ስትወጣና ስትገባ ምንግዜም ቢሆን የእኔን ፍቅር ከማስታወስ አትቆጠብ።” ይለዋል። አገልግሎት ግዴታ ሳይሆን ፍቅር ነው። አገልግሎት እርግማን ሳይሆን ምሕረት ነው። አገልግሎት ቅጣት ሳይሆን ቸርነት ነው። አገልግሎት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር፣ ምሕረትና ቸርነትን የምናስተላልፍበት ስለሆነ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እርሱን ይመለከተዋልና ቁልፉን በእጁ ያዘ። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

ሌላው ነጥብ ራእይ 3:7 ላይ ያለው ሃሳብ ነው። ይህ ክፍል ከትንቢተ ኢሳይያስ 54:22-25 ይጠቅሳል። በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገሩለት የዳዊት መክፈቻን የሚይዘው፣ የንጉሡን ግምጃ ቤት የሚቆጣጠረው ሊሰጥም ሊነሳም ሥልጣን የተሰጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ መስጠትም መንሳትም ማሳጣትም ማስገኘትም የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ አገልጋይ መጠበቅ ያለበት፣ የግምጃ ቤቱ ቁልፍ ካለው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሊሆን ይገባዋል። በዚህ ውስጥ ጨምረን መገንዘብ የሚኖርብን፣ ለአገልግሎት የሚያስፈልጉትን ከቁሳቁስ ጀምሮ እስከ መንፈሳዊ ኃይል ድረስ፣ አንድ አገልጋይ ማግኘት የሚቻለው የሰማያዊውን ሆነ የምድሩን ግምጃ ቤት ቁልፍ የያዘውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ደጅ ሲጠና ብቻ ነው። ቁልፉ በጌታ እጅ ነውና። ለጌታ ኢየሱስ ክብርና



አገልግሎት እስከ ሆነ ድረስ ሰማያዊም ሆነ ምድራዊ በረከት ከጌታ ይዘንባል፤ ይቀርባል፤ ይጎርፋልም። ስለዚህ አንድ አገልጋይ ከጌታ ኢየሱስ የሆነ መልእክትን ከያዘና ከወጣ፣ ለአገልግሎቱ መሳካት የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር የማሟላት ኃላፊነቱን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይወስዳል። አገልጋይ ለአገልግሎቱ የሚያሻውን ለመጠየቅ የልጅነት መብትና ነጻነት ከአምላኩና ከጌታው ዘንድ አለው። የአንድ ንጉሥ ግምጃ ቤት ብልጽግና ለሰብዐዊ አዕምሮ እጅግ አግራሞትን የሚፈጥርና የሚያስደንቅ ከሆነ የመንግሥተ ሰማይ ግምጃ ቤት ሲከፈትና ብልጽግናው ሲታይ ለመግለጽ ቃላትም የሚኖሩለት አይደለም፤ እጅግ እፁብ ነው። ግን አንድ አገልጋይ በዚህ ግሩም በሆነው በረከት ሳይሆን ዓይኑን ማሳረፍ ያለበት፣ ቁልፉን በያዙት በእጆቹ ላይ ያለውን የፍቅር ማህተም የሆነችውን የቁስሏን ምልክት ብቻ ሊሆን ይገባል። የግምጃ ቤቱ መከፈትና የበረከቱ መፍሰስ ምክንያት የጌታ ኢየሱስ ፍቅር እንደ ሆነ አንድ አገልጋይ መዘንጋት ከጀመረ ሕይወቱም ሆነ አገልግሎቱ በአደጋ ላይ ነውና ዓይኖቹን ፈጥኖ ከበረከቱ ላይ አንስቶ፣ የጌታ ኢየሱስን የእጆቹን ቁስሎች ምልክት ማየት ተገቢው ነው። በዘመናችን ታላላቅ አገልጋዮችን ውጦ ያስቀረው ትልቁ ድካም ቢኖር “የብልጽግና ወንጌል” በማለት በተሳሳተ አመለካከት የሚካሄደው እንቅስቃሴ ነው። ጌታ ለአገልጋዮቹ ለአገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን በሙላት ለመባረክ ፈቃዱ ሆኖ ሳለ፣ ግን ያንን ባርኮት ለወንጌል ሳይሆን ለራሳቸው በማድረግ በዓለማዊነት ተውጠው የቀሩ በርካታ ናቸው። ይህም ችግር የሚመጣው ከላይ እንደ ገለጽነው፣ ዓይንን በጌታ ቁስል ላይ አድርጎ ፍቅሩን ከማስታወስ ይልቅ፣ ዓይንን በንዋይ ላይ አድርጎ በዓለማዊ ብልጽግና በመዋጥ የሚመጣ ድካም ነው።

የእግዚአብሔርን አሠራር ለመረዳት፣ የክርስቶስን ውበት ከመመልከት፣ የክርስቶስን ብቃት ከማስተዋል፣ በክርስቶስ ያለውን ቁልፍ ከማየት ባሻገር አርቀን ማየት ይኖርብናል። ይህንን ከባለራእዩ ከዮሐንስ የራእይ ልምምድ መገንዘብ እንችላለን። በራእይ 1:2 እና 3 ላይ

ዮሐንስ ራእይን ከተመለከተ በኋላ በዚያ ሳይገደብ እንደ ገና ከዚያ አርቆ የማየትን ዕድል እንዳገኘ ከዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ያለውን እውነት በመረዳት መገንዘብ እንችላለን።

ዮሐንስ በራእዩ ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ርቆ ሲሄድ እንመለከታለን። ጌታ ኢየሱስን በምድር ላይ ከአብያተ ክርስቲያናት ድካም ጋር ብቻ አይቶ አልቀረም፤ አንድ ባለ ራእይ በምድር ላይ የሚገኘውን ምስቅልቅል አሠራር ብቻ ተመልክቶና ለዚያም መፍትሔ የሆነውን ክርስቶስ እንደ ሆነ አውቆ ብቻ በዚያ ላይ ረግቶ መቆም አይገባውም። እንደ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ የማየት ትዕግሥት ዕድል ሊኖረው ይገባል። እውነተኛ ራእይ ምድርንና ሰዎችን ብቻ አሳይቶ አያበቃም። ከዚያ ባሻገር ያለውን እግዚአብሔርን፣ ዙፋኑን፣ ክብሩን፣ ድንቁንና ግርማ ሞገሱን ያሳየናል። ይህም ትዕይንት በቀጥታ እግዚአብሔርን እንድናመልክ፣ ለእርሱ እንድንሰግድ፣ በግርማ ሞገሱ እንድንገረም፣ በጽድቁ እንድንታመን ለክብሩ እንድንንቀጠቀጥ ያደርገናል፤ እነዚህን ሁሉ በእውነትና በሐሴት እያደረግን የምንመለከተው ይህ እውነተኛው ራእይ ነው።

ዮሐንስ በራእዩ በአምስተኛው ምዕራፍ ላይ፣ በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ በመንፈስ ተነጥቆ ከተወሰደ በኋላ፣ የተገነዘበው ነገር ቢኖር ሰው ሰራሽ ክልሎች ቦታ እንዳልነበራቸው ነው። በማቴዎስ 28 ላይ እና በሐዋርያት ሥራ 1 ውስጥ፣ ጌታ ኢየሱስ ታላቁን ተልእኮ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ አገልግሎታቸው በክልል በፖለቲካ ድንበርና አኗኗር እንዳይወሰን በማሰብ በኢየሩሳሌም በይሁዳ፣ በሰማሪያ ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ የደህንነቱን መልእክት ያደርሱ ዘንድ አዝዟቸዋል። ዮሐንስም በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ ከተመለከታቸው ታላላቅ እውነቶች ይኼኛው አንደኛው ነው። መንግሥተ ሰማያት ክልል አልባ ሆኖ፣ በነጻነት የሚመላለስባት ሰማያዊ መንግሥት ሆኖ ነው ያገኛት። ከዚያ በኋላ ታዲያ ዮሐንስ ክልልን ጥሶ፣ ድንበር አልባ በሆነ ግዛት ውስጥ በመሆን የተከፈተውን መጽሐፍ ለማንበብ



እድሉን አገኘ። እኛም በሕይወታችን ከደረጃ ወደ ደረጃ አድገንና ተሸጋግረን የሕይወትን ታላቅ ምስጢር የምንገነዘበው፤ ራሳችን ተብትበን ካጠርነው የክልል ወጥመድ ስንወጣና ነጻ ስንሆን ብቻ ነው፤ አለበለዚያ አገልግሎታችን በክልል ከመወሰኑ ባሻገር፣ ይበልጥ የጌታ ኢየሱስን ራእይና ምስጢርን የሚገልጽልንን ሰማያዊውን መገለጥ የሚያስገነዝበንን መጽሐፍ ከማንበብ እንገታለን፤ ከመረዳትም እንታቀባለን።

ዮሐንስ በምዕራፍ 4 ላይ እግዚአብሔርን በግርማ ሞገሱ በታላቅነቱና በኃይሉ በዙፋኑ ላይ ሆኖ ሲመለከተው፣ እርሱ በምላሹ ያደረገው ነገር ቢኖር፣ የአምልኮ መስዋእትን በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮና ወድቆ ማቅረብ ነበር። ከዚያ በኋላ በአምስተኛው ምዕራፍ ላይ የተከፈተውን መጽሐፍ ሲያነብ እንመለከታለን። አዎ! የእግዚአብሔርን ምስጢር ለመረዳት የሚያስችለንን የተከፈተውን መጽሐፍ ማንበብ የምንችለው፣ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ተረድተንና በፊቱም ወድቀን አምልኮን ካቀረብን በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት ምንም የሚገልጽልን ሰማያዊ ምስጢር የለም።

ለመሆኑ እውነተኛ አምልኮን ለእግዚአብሔር ካቀረብን በኋላ፣ የተከፈተውን መጽሐፍ ስንመለከት በውስጡ የምናነበው ምንድነው? አዎ! በውስጡ የተዘረዘረው የጌታ የኢየሱስ ገድልና ሥራ ነው። “ታርደሃልና፣ ከወገንም ከቋንቋም ከነገድም ሰዎችን ለራስህ ሰብስበሃልና፣ ለይተሃልና” ይለዋል። ስለዚህ እኛም እግዚአብሔር ራእይን የሚሰጠን፣ ጌታ ኢየሱስ የሞተላቸውን የቆሰለላቸውንና የደማላቸውን ሕዝቦች፣ በወገናዊነት፣ በጐሰኝነት በጠባብነት ክልል ሳንወሰን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንሰበስብ ነው። ይህ ነው የዚያ ታላቅ መጽሐፍ ቀዳሚ መልእክት። በ6ኛው ምዕራፍ ላይ በዮሐንስ ራእይ እንደምንመለከተው ወደ ዓለም ሁሉ በሁሉም አቅጣጫ መድረስ እንዳለብን የሚያስረዳን ምስጢር ነው።

ራእይን በማስተዋል በመታዘዝ እንዲያድግ ማድረግ ሌላው በራእይ የማደግ ምስጢር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን እውነት አጽንኦት

ሲሰጠው "ከሰማይ ለታየኝ ራእይ እምቢ አላልኩም።" በማለት ነው መታዘዙን የገለጸው። በራእይ ለማደግና፣ በሰማያዊው ራእይ ለመኖር ከተፈለገ ለራእዩ መታዘዝ ምንም አማራጭ የማናገኝለት መንገድ ነው። ከዚያም ዘልቆ ያየነውን ሰማያዊ ራእይ ተጨባጭና፣ ገሃድ ወጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ከተፈለገ መከተልና ማድረግ የሚገባን አራት መሠረታዊ አደራረጎች አሉ። እነርሱም ማየት፣ ማቀነባበር፣ ማብራራትና ማሳደግ ናቸው። እነዚህ አራቱ መሠረታዊ አደራረጎች በኤፌሶን 4:11 ላይ ከተጠቀሱት ዓበይት የአገልግሎት ምድቦች ወይም የአገልግሎት ጸጋዎች ጋር እጅጉን የተቆራኘ ባሕርይ አላቸው። ይኸውም ነቢያቶች ያያሉ፣ ሐዋርያቶች በነቢያት የታየውን ራእይ ተቀብለው ያቀነባብራሉ፣ መሠረትንም ጥለው የአስተዳደርን ሥርዓት ያበጃሉ። አስተማሪዎች ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠውን ነቢያት የተመለከቱትን፣ ሐዋርያት አቀናብረው መሠረት የጣሉትን ራእይ ያብራራሉ፣ ይገልጣሉም። እረኞች ደግሞ የታየውን፣ የተቀነባበረውንና፣ የተብራራውን ራእይ ተቀብለው መንጎቻቸውን ያሳድጋሉ፣ ይጠነቀቃሉ። ማለት ነው። ስለዚህ የነቢይ ዓይነ ልቦና የሐዋርያት መሠረት፣ የአስተማሪዎች ጸጋን የተሞላ አእምሮ፣ የእረኞች የፍቅር ልብ፣ ለራእይ ዕድገትና ፍጹምነት እጅግ አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። ራእይ በነዚህ አራት ደረጃዎች እንደ ሰንሰለት ተያይዞ ካልተሸጋገረ በእንጭጭነቱ ይቀጫል አለዚያም ፍጹም ሆኖ ተጨባጭነት ሳይኖረው በሃሳብ ደረጃ ይቀራል። ዋጋም አይኖረውም።



# ም ዕ ራ ፍ   አ ሥ ራ   አ ን ድ

## የ ማ ጠ ቃ ለ ያ   ሃ ሳ ብ



## በ አ ገ ል ግ ሎ ት   ማ ደ ግ

አገልግሎት ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ፈቃድ በሙሉ ልብ መታዘዝ ስለሆነ በሥጋ እስካለን ድረስ መታዘዛችን ፍጹም ነው ማለትን አንደፍርም። ይሁን እንጂ ከእርሱ ጋር በመታዘዝ ለእርሱ መኖራችን በየጊዜው እየጨመረ መሄዱ የግዴታ ነው። እንግዲህ "በአገልግሎት ማደግ" ብለን የምንጠራው ይህን ዓይነት ሂደት ነው። በሕይወታችንም ሆነ በአገልግሎት እንድናድግ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ እሙን ከሆነ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በጣም ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት።

አንደኛ አገልግሎትን ለይቶ መቀበል። የአገልግሎት ጥሪአችንን ለይተን ካልተቀበልን በሙሉ ልባችን ለጥሪው መስጠት ስለማንችል የአገልግሎታችን ጥራቱና ጥልቀቱ ይህን ያህል አይሆንም። ከዚህም የተነሳ

ጥሪዬ ብለን ባልያዝነው አገልግሎት ማደግ አዳጋች ይሆናል። ስለዚህ የአገልግሎት እድገት መሠረቱ ከጌታ የተሰጠንን አደራ ለይቶ ተቀብሎ በታማኝነት ማገልገል ነው።

ሁለተኛ ለአገልግሎቱ የጠራንን ጌታ ማወቅ። የጠራንን ጌታ ታላቅነቱን፣ ምህረቱን፣ ቸርነቱን፣ ፍቅሩን፣ ርኅራኄውን፣ ይቅር ባይነቱን፣ ቅድስናውንና ንጽህናውን ካልተገነዘብን በተቀደሰው አገልግሎት ማደግ አስቸጋሪ ይሆናል። የእርሱን ማንነት በተረዳን ቁጥር የተሰጠንን ሃላፊነት በአክብሮት እንይዛለን። ጥሪታችንም እርሱን ለማስከበር ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

ሦስተኛ ለማደግ ፈቃደኛ መሆን። መንፈሳዊ እድገት የግለሰብን ፈቃደኝነት ይጠይቃል። የማደግ ፍላጎት ካለ እድገት ከግቡ ደርሶ ለማየት ስለምንፈልግ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አንልም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚፈልግ እንደሚያገኝ፣ ለሚያንኳኳ እንደሚከፈትለት፣ ለሚጠይቅ እንደሚሰጥ፣ ጽድቅን የሚራብ እንደሚጠግብ የሚያረጋግጠው በመንፈሳዊ እድገት ውስጥ የእምነት እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ለማሳየት ነው።

አራተኛ የሕጻንነትን ጠባዮች ለመሻር ፈቃደኛ መሆን። አዲሱን ለመቀበል አሮጌውን ማስቀመጥ ወይም ወደ ፊት ለመሮጥ ያለፈውን መተው አስፈላጊ ነገር ነው።

አምስተኛ የግል ድካማችንን ማወቅ። ሰው በሽታውን ካላወቀ መድኃኒት አያገኝም። ድካማችንን ለይተን በማወቅ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካላስወገድን ማደግ አንችልም።

ስድስተኛ የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ጆሮን መስጠት። እግዚአብሔርን ካልሰማን ማደግ አንችልም። የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ በሙሉ ልብ መታዘዝ ለአገልግሎት እድገት መተኪያ የሌለው ነገር ነው።

ሰባተኛ ለተገለጠ: ለእግዚአብሔር እውነት መኖር። ለተገለጠልን ለእግዚአብሔር ቃል ካልኖርን በአገልግሎት ማደግ አስቸጋሪ ነገር



ይሆናል።

ስምንተኛ የቅዱሳንን ምክር መቀበል። እግዚአብሔር ለእድገታችን በተለያየ መንገድ ይናገራል። ከእነዚህ አንዱ በእግዚአብሔር ሰዎች በኩል ነው። ለማደግ የሚፈልግ አገልጋይ የቅዱሳንን ድምጽ ሳይንቅ የሚሰማውን መርምሮ ከጌታ የሆነውን ለይቶ መቀበል ይኖርበታል።

ዘጠነኛ ከሁሉም የሚበልጠውን የአገልግሎት መንገድ ለይቶ ማወቅ። ከሁሉም የተሻለ የአገልግሎት መንገድ ድርጊት ሳይሆን በፍቅር መኖር ነው። ጥሪያችን እግዚአብሔንና የእግዚአብሔርን ሰዎች እንድንወድ ነው። የአገልግሎት እድገት በፍቅር ማገልገል ብቻ ሳይሆን በፍቅር ምክንያት ማገልገል ነው። ለሚያድግ አገልጋይ የአገልግሎት መጀመሪያው ሆነ መጨረሻው ፍቅር ነው። "ፍቅር ግን ከሌለኝ ..." (1ቆሮ. 13:1)

አሥረኛ የአገልግሎት እድገት እንቅፋቶችን ለማስወገድ ፈቃደኛ መሆን። እድገት የተፈጥሮ ሂደት ቢሆንም ይህን ግስጋሴ ማደናቀፍ የሚችሉ ብዙ ማሰናከያዎች አሉ። በአገልግሎቱ ማደግ የሚፈልግ አገልጋይ እነዚህን ነገሮች ለይቶ ከአገልግሎቱም ሆነ ከሕይወቱ ማራቅ ይገባዋል። ብዙ ጊዜ የራሳችንን ሁኔታ ስንመረምር ለአገልግሎት ሕይወታችን እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች የሚከተሉትን ይጨምራል:-

1▸ ደርሻለሁ ብሎ በአገልግሎት ውስጥ መዝናናት መጀመር።

2▸ የአገልግሎትን ጥሪ የእድገት መጨረሻ አድርጎ መገመት።

3▸ ከሌላ ለመማር ፈቃደኛ ያለ መሆን።

4▸ መንፈሳዊ ኩራት።

5▸ ምክር ያለ መቀበል።

6▸ ያለ ማንበብና ያለ ማጥናት (መንፈሳዊ መጻሕፍትን ያለማንበብና ያለ ማሰላሰል)።

7▸ በቃሉ ጥናትና በጸሎት ያለ መትጋት።

8▸ የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግን ችላ ማለት።

9▸ ካለፈው ያለ መማር።

10▸ ነገርን አርቆ ያለ ማየት።

11▸ ቆም ብሎ አገልግሎትን ያለ መመዘን።

12▸ ከሌሎች ጋር ራስን ማወዳደር።

13▸ አገልግሎትን እንደ ድርጊት መውሰድ።

14▸ የሌሎችን ቅባትና ጸጋ መናቅ።

15▸ በቅሬታ መኖር ወይም ቂም መያዝ።

16▸ በተከከር መንፈስ መኖር።

17▸ የመጀመሪያን ፍቅር ቸል ማለት።

18▸ የአገልግሎትን ውለታ መቁጠር።

19▸ ምስጋና ቢስ መሆን።

20▸ ሁልጊዜ እንደ ትላንትና ለማገልገል መሞከር ናቸው።

እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ ለአገልግሎት እድገት እንቅፋቶች ናቸው። አንተ በእነዚህ ነገሮች የራስህን አገልግሎት ብትመዝን የት ነው የምትሆነው?

## በ ራ እ ይ  ማ ደ ግ

እንግዲህ በራእይ ማደግና ራእይን ተጨባጭ ለማድረግ መለኮታዊን ራእይ እንደሚገባ መረዳት መሠረታዊ ነገር ነው። ከዚህ አንጻር:-

ራእይ፣ እግዚአብሔርን ማየት

ራእይ፣ እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት

ራእይ፣ እግዚአብሔር እንደሚያይ ማየት

በራእይ ማደግ፣

▸አርቆ ማየት

▸የሚታየውን ነገር ተጨባጭ ማድረግ

▸የሥጋን አመለካከት ማስወገድ

▸ሰማያዊውን ከሥጋዊው ራእይ መለየት



▸ሰማያዊውን ራእይ ጨብጠን ለዚያ ለሰማያዊ ራእይ መኖር። ይህ ማለት ለሰማያዊ ራእይ ታዝዞ መኖር ማለት፣ ከስድነት፣ ከዓላማ ቢስነት፣ ከአቅጣጫ ቢስነት ነጻ መውጣት ማለት ነው። ሰማያዊ ራእይ ዓይንን ይከፍታል። ለሰማያዊ ራእይ ዓይናችን ከታወረ፣ የሥጋዊ ዓይናችንም አደጋ ላይ ነው። ለዚህ ዋነኛ ምሳሌ የሚሆነን የሶምሶን ሕይወት ነው። ሶምሶን ሰማያዊውን ራእይ ረሳ፣ ቸል አለ። ይህ እንግዲህ ለሰማያዊው ራእይ መንፈሳዊ ዓይንን ማሳወር ማለት ነው። ሶምሶን በዚህ ቸልተኝነቱና መንፈሳዊ ዕውርነቱ የተነሳ እጆቹን ለጠላቶቹ አሳልፎ ሰጠ። ከዚያም ጠላቶቹ አስቀድመው የወሰዱበት እርምጃ ዓይኑን ማውጣት ነበር። የሥጋዊ ዓይንም አደጋ ላይ መውደቅ ማለት ደግሞ ይህ ነው። ከዚያም የሶምሶን ጠላቶች እጆቹን በሰንሰለት አስረው ጉልበቱ ለእነርሱ እንዲንበረከክ አስገደዱት። የእግዚአብሔርን ራእይ ቸል በማለት በንዝህላልነት የምንመላለስ ከሆነ፣ ቅጣቱ የሚጀምረን በዚሁ በምድር ላይ ነው፤ ትልቅ ጉዳት አለበት።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰጠን ራእይ በመጠንቀቅ ወደ ፊት መገስገስ በጣም አስፈላጊ ነው። በራእይ ማደግን ሰፋ አድርገን ሊመጣ ያለውን ነገር ማለት የወደፊቱን አይተን “...የሰማዩ አምላክ ያከናውንልናልና፣ እኛም ባሪያዎቹ ተነስተን እንሠራለን፤...” ማለትን መቻል ነው። (ነህ. 2:20) መንፈሳዊ ራእይ ከሩቁ እንደሚታይ የተራራ ሰንሰለት ነው። ከርቀት አንድ ይመስላል በቀረብን ቁጥር ግን አንዱ ተራራ ከሌላው ያለው ርቀት ግልጽ እየሆነ ይሄዳል። መንፈሳዊ ራእይም እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር እንድንደርስበትና እንድናከናውነው በሩቁ ያሳየናል። በቀረብን ቁጥር ቅደም ተከተሉ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል። በዚህ ውስጥ ሁለት በጣም አስፈላጊ ነገሮች አሉ።

አንደኛ▸ ዓይናችንን አንስተን ጌታ የሚያሳየንን ማየት መቻል ነው። ትኩረቱ በዛሬ ችግርና ሥራ ላይ ብቻ የሆነ አገልጋይ የወደፊቱን ማየት አይችልም ወይም ይቸገራል። ጌታ ኢየሱስም ሐዋርያት የመንግሥቱን

ሥራ ማየት አቅቷቸው ለቀኑ በሚሆን ምግብ ብቻ ላይ በጣም ባተኮሩ ጊዜ ይህ አደገኛ መሆኑን ለማሳሰብ እንዲህ አላቸው:- "እናንተ:- ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፣ ዓይናችሁን አንሱ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ።" (ዮሐ. 4:35)

ሁለተኛ▸ በራእይ ለማደግ መጀመሪያ የደረስንበት ወይም ጌታ ግልጽ አድርጎ ያሳየንን በሥራ ላይ ማዋል ነው። ይህን ሳናደርግ ወደ ሌላ ካለፍን የነገሩ ቅደም ተከተል ከመዛባቱ በላይ በእግዚአብሔር አሠራር ሳይሆን በራሳችን ዘዴ መሥራት ስለምንጀምር የሥጋ ሥራ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ራእይ ማሳደግ አይቻልም።

ሦስተኛ▸ በራእይ ለማደግ ከአንዱ ተራራ ወርደን ወደሚቀጥለው ላይ መውጣት ያስፈልጋል። እላይ እንደ ተጠቀሰው እግዚአብሔር የሚያሳየን ራእይ እንደ ተራራ ሰንሰለት የተያያዘ ነው።






አንዱ ወደ ሌላው ያሳድጋል። ችግሩ ግን የመጀመሪያውን ራእይ በሥራ ላይ አውለን ከተባረክንና ከተሳካልን ከዚያ ተራራ ጫፍ ወደ ሌላው መዝለልን እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ ነገሩ እንደዚያ አይሠራም። ወደ ሁለተኛ ተራራ ወይም ወደ አገልግሎት ራእይ ለመግባት ከመጀመሪያው ወርደን ወደሚቀጥለው መውጣት ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ለራእይ እድገት እንቅፋት የሚሆነው ይህ ነው። ወርደን እንደገና ወደሚቀጥለው ከመውጣት ይልቅ እዚያው መቆየቱን እንመርጣለንና። ስለዚህ ነው ሌሎችን ለአገልግሎት ማዘጋጀትና ሃላፊነቱን ማስተላለፍ በጣም የሚከብደን። ወርዶ መጀመር ራስን ዝቅ ማድረግ ይጠይቃል። ይህ ለራእይ እድገት ምሰሶ ነው። ይህም ስለሆነ በራእይ ለማደግ እንደ ጳውሎስ "አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፣ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ፣ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።" (ፊል. 3:12-14) ማለት መቻል አለብን።

## ደ ራ ሲ ው   ያ ሳ ተ ማ ቸ ው   መ ጻ ሕ ፍ ት

1▸ ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ (የመጀመሪያው እትም)

2▸ አገልግሎትና የጽድቅ አክሊል ለመንፈሳዊ መሪ

3▸ ከዚህም የሚበልጥ

4▸ አገልግሎትና የጽድቅ አክሊል

5▸ ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ (ሁለተኛው እትም)

6▸ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ

7▸ በአገልግሎትና በራእይ ማደግ

ETHIOPIAN [illegible] CHURCH
[illegible] RD.
DALLAS, TX 75210





ወንድማችን ዶ/ር አለሙ ቢፍቱ የጌታ ኢየሱስ ወንጌል ሰባኪ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ፣ የመንፈሳዊ መጻሕፍት ደራሲና መሪዎችንና አገልጋዮችን ለማሠልጠንና ለማደራጀት እግዚአብሔር ከባድ ሸክም የሰጣቸው የክርስቶስ ባሪያ ናቸው። ገና ወጣት ሆነው ኢትዮጵያ በነበሩበት ጊዜ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ መንፈሳዊ ድርጅቶችና ስብሰባዎች ላይ በሰጡት አገልግሎት ብዙዎቻችን ተባርከንበታል፣ አድገንበታልም። ወደ አሜሪካም ከመጡ በኋላ እግዚአብሔር ከመካከላችን ካስነሳቸው መሪዎች አንዱ ስለሆኑ በየቦታው በመዘዋወር ያልተቆጠበ አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው።

ዶ/ር አለሙ ከሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪአቸውን አግኝተው በዚሁ ዩንቨርሲቲ ውስጥ ረዳት ፕሮፌሰር ሆነው ለሦስት ዓመት ተኩል ሠርተዋል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ኮምፓሽን ኢንተርናሽናል በተባለው ክርስቲያን ድርጅት ውስጥ የመሪዎች አሠልጣኝ በመሆን በዓለም ዙሪያ አገልግሎታቸውን ይሰጣሉ።

በተጨማሪ ባለፉት ሦስት ዓመታት እግዚአብሔር የሰጣቸውን የአግልግሎት ራእይ በመከተል "የክብሩ ወንጌል አገልግሎት" የተባለውን መንፈሳዊ ድርጅት መሥርተው መንፈሳዊ መጻሕፍትን በመጻፍና የትምህርት ካሴቶችን በማዘጋጀት እንዲሁም ለመንፈሳዊ መሪዎች አውደ ጥናቶችን በመስጠት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያገለግላሉ። ይህን ድርጅት እግዚአብሔር የበለጠ እንዲጠቀምበትና ለብዙዎች በረከት እንዲያደርገው ሁሉችንም በጸሎት፣ በሃሳብና በተለያዩ መንገዶች አብረናቸው እንቁም።

ዶ/ር አለሙና ባለቤታቸው ወ/ሮ ገነት ያዕቆብ ከሁለት ልጆቻቸው ኪያና አማኑኤል ጋር የኮሎራዶ ነዋሪ ናቸው።

መንግሥቱ ለማ